# የመድን ሰጪና የመድን ገቢ መብትና ግዴታዎች በኢትዮጵያ ሕግ

ዘካርያስ ቀነዓ*

## መግቢያ

መብትና ግዴታ በስፋትና በጠባቡ ሊታዩ የሚችሉ ፅንሰ ሐሳቦች ናቸዉ:: በዚህ ጽሑፍ ዉስጥ ግን መብትና ግዴታ ከሕግና ከዉል ረገድ ካላቸው ጠባብ ቴክኒካዊ ትርጉም አንፃር እንደሚታዩ ለአንባቢ ግልጽ ሊደረግ ይገባል።

መብትና ግዴታ ሁለት አብረው የሚሄዱ /ኮሪሌቲቭ/ ፅንስ ሐሳቦች ናቸዉ:: መብት ሲባል አንድ ሰው ከአንድ የተለየ ሌላ ሰው ወይም ባጠቃላይ ከአንድ ማሕበረሰብ ወይም ከአንድ ሕብረተሰብ ሊያገኝ የሚገባው ገንዘብ፣ አገልግሎት ወዘተ ሲሆን ባንፃሩ ደግሞ ለባለመብቱ እንዲደርሰው የሚፈለገውን ገንዘብ ወይም አገልግሎት ወዘተ የመስጠት የማቅረብ ግዴታ በዚያ በተለየ አንድ ሰው ላይ ወይም ባጠቃላይ በማኀበረሰቡ ወይም በሕብረተሰቡ ላይ እንደሚወድቅ እናያለን።

መብትና ግዴታ የሚመነጩት ከሕግ ወይም ከውል እንደመሆኑ መጠን በዚህ አነስተኛ ጽሑፍ ውስጥ በተቻለ መጠን በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ውስጥ ለመድን ውል ተዋዋይ ወገኖች የተሰጣቸውን አንዳንድ መብቶችና በዚህ አንፃር የተጣለባቸውን ግዴታዎች በመድን ውሎች ውስጥ ሰፍረው ከምናገኛቸው ጋር በማነፃፀር ለመመልከት ሙከራ ይደረጋል።

መብትና ግዴታ ከሕግ ሳይሆን ከውል በሚመነጩበት ጊዜ የግድ አዛዥ የሕግ አንቀጾችን ሳይጥሱ ወይም ሳይቃረኑ መቋቋም እንዳለባቸው ግልጽ ቢሆንም ማስታወሱ ጠቃሚ ነዉ። በዚህ ረገድ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር (ከዚህ በኋላ የፍ.ብ.ሕ.ቁ.) 1731/2/ ተዋዋይ ወገኖች ከውላቸው እንዲመነጩ የሚፈልጉትን መብቶችና ግዴታዎች አዛዥ የሕግ አንቀጾችን ሳይጥሱ ወይም ሳይቃረኑ እንደፈለጉ ማቋቋም ወይም መመሥረት እንደሚችሉ ይደነግጋል።

የዚህ ጽሑፍ ርዕስ የመድን ውል ተዋዋዮችን መብትና ግዴታ የሚመለከት ቢሆንም በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ውስጥ በዚህ ርዕስ ሥር ሊነሱ የሚችሉትን ጉዳዮች ሁሉ በእንደዚህ ዓይነቱ ውስን ጽሑፍ መዳሰስ አይቻልም። ስለሆነም ይህ ጽሑፍ የቃኛቸው በርዕሱ ውስጥ ሊጠቃለሉ ከሚችሉ ጉዳዮች ጥቂቶቹን ብቻ ያዉም በንግድ ሕጉ ዉስጥ በጠቅላላ ድንጋጌነት የሰፈሩትን መሆኑን አንባቢያን ከወዲሁ እንዲገነዘቡት ያስፈልጋል።

## ተዋዋይ ወገኖች እነማን ናቸው?

ከመድን ሕግና ውል አኳያ "ተዋዋይ ወገኖች" ሲባል በአንድ በኩል የመድን ሽፋን እንዲሰጠው ለመድን ሰጪው አመልክቶ ማመልከቻው ወይም ጥያቄው ተቀባይነት

*ተባባሪ ፕሮፌሰር እና ተ/ዲን አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ሕግ ትምህርት ቤት

ያገኘ በሕግና በፖሊሲዎች ውስጥ መድን ተቀባይ ወይም መድን ገቢ የሚባለው ወገንና በሌላ በኩል የመድን ሽፋን ለመስጠት የተዋዋለው መድን ሰጪ ብቻ መስለው ሊታዩ የሚችሉ ቢሆንም በንግድ ሕጉ ውስጥ እንደተመለከተው "ወኪል" "ፈራሚ" "የመድን ውል የተላለፈለት ሰው" መድን የተገባለት ንብረት የተላለፈለት ሰው "ወራሽ" "ተጠቃሚ" ተብለው በተለያዩ ቁጥሮች ሥር በተለያየ አገላለጽ የተጠቀሱ ሌሎችም ምናልባት ከመብትና ግዴታ አንፃር ከመድን ገቢዎች ጋር የሚደመሩ ሰዎች መኖራቸውን እንመለከታለን፡፡ በዚሁ መሠረት በንግድ ሕጉ የመድን ድንጋጌዎች ባብዛኞቹ ላይና በፖሊሲዎች ላይ መድን ገቢ፣ ተጠቃሚ፣ የመድኑ ውል ባለቤት ወዘተ በሚል አጠራር የተመለከቱት የሚናገሩት ያው ስለመድን ገቢ መሆኑን መረዳት ጥሩ ነው፡፡[1]

## የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ ከውሉ ምሥረታ ጋር በተያያዘ

የመድን ውልን ምሥረታ በሚመለከት ምንም እንኳን የመድን ውል ልዩ ውል ቢሆንምና የንግድ ሕግ ቁጥሮች 654-712 በልዩነታቸው በቅድሚያ ተፈፃሚ ቢሆኑም በፍ.ብ.ሕ.ቁ.1676/1/ እና /2/ መሠረት የመድን ውሎችም ጠቅላላ ውሎችን በሚመለከቱ የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ይገዛሉ፡፡ በመሆኑም የውል አቀራረብና አቀባበልን የሚመለከቱ የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች፣ እንዲሁም የተዋዋይ ወገኖች የችሎታ፣ በውል ለመገደድ ፈቃዳቸውን በነፃ የመስጠት፣ የውሉ ጉዳይ ማለትም የተዋዋይ ወገኖች ግዴታዎች ጥርት ባለ ሁኔታ መመልከት፣ የተዋዋይ ወገኖች ግዴታዎች የሚቻሉ፣ ሕጋዊና ከኀብረተቡ የሞራል ሕግ ጋር የማይጋጩ፣ እንደዚሁም ውሉ ሕግ በሚያዘው ፎርም[2] መሠረት የተቋቋሙ መሆን እንዳለባቸዉ ስናስተውል፣ ከነኚህ በሕግ ፊት የፀና ውል እንዲቋቋም አስፈላጊ ናቸው ተብለው ከሚወሰዱት ነገሮች ያንደኛው አለመሟላት አንድን የመድን ውል በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1808 እና ተከታታዮቹ ቁጥሮች መሠረት ፍርስ ወይም ፈራሽ ሊያደርገው ይችላል፡፡

በንግድ ሕግ ቁጥር (ከዚህ በኂላ ን.ሕ.ቁ.) 654/1/ እንደተመለከተው የመድን ውል ማለት፣

- ኢንሹራንስ /መድን/ ሰጪ የሚባለው /ወገን/፣

---

[1] ከሕይወት መድን አኳያ "ተጠቃሚ" የሚለው ቃል "beneficiary" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ትርጉም ሆኖ በጠባቡ መወሰዱን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

[2] በን.ሕ.ቁ.657/1/ መሠረት አንድ የመድን ውል የመድን ውል ፖሊሲ በሚል ጹሑፍ መደገፍ አለበት፡፡ የን.ሕ.ቁ.657/2/ እንደሚደነግገዉ አንድ የመድን ውል ፖሊሲ ሲሻሻልም እንደዚሁ "ተጨማሪ ጹሑፍ" /endorsement/ በሚባል ጹሑፍ መሆን አለበት፡፡ ተጨማሪ ጹሑፍ እስከሚፈረም ድረስ መድን ሰጪው ጊዜያዊ የመድን ሽፋን መስጠቱን የሚያረጋግጥ የጽሑፍ ውልም ሊሰጥ እንደሚችል በን.ሕ.ቁ. 657/3/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በን.ሕ.ቁ. 657/3/ የሚሠጠው ሰርቲፊኬት በሌሎች አገሮች "Cover note" የሚባለው መሆኑ ነው፡፡

- በአንድ ጊዜ ወይም ስለአከፋፈሉ በተስማሙት መሠረት ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲከፈል የተመደበውን አረቦን /ፕሪሚዬም/ ተቀበሎ፣
- በውሉ የተመለከተው አደጋ ወይም ቀን፣ ወይም ኃላፊነት በደረሰ ጊዜ፣
- መድን ለገባው ሰው ወይም ለተጠቃሚው ወይም የመድን ውል መብት ለተላለፈለት ሰው በውሉ የተመለከተው የኃላፊነት ጣሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ በደረሰው ጉዳት ልክ ካሣ ወይም በውሉ የተመለከተውን ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ውል ሲሆን፣

የውሉን ጉዳይ (object of the contract) ለይተን ለማውጣት ብንሞክር በመድን ሰጪው በኩል ስምምነት የተደረገበትን አረቦን (premium) የማግኘት ጉዳይ ሲሆን በመድን ገቢው በኩል ደግሞ የተፈራው አደጋ ወይም ጊዜ ወይም ኃላፊነት ሲደርስ የመካስ ወይም የተመለከተውን ገንዘብ የማግኘት ፍላጐት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በዚሁ መሠረት መድን ሰጪው ዋስትና ሊሰጥበት እየተዋዋለ ያለውን የአደጋውን (risk) መጠንና ሁኔታ አመዛዝኖ በስሌት የደረሰበትን አረቦን የመቀበል መብት ሲኖረው፣ መድን ተቀባዩም ይህንኑ የመክፈል ግዴታ ይወድቅበታል፡፡

ምንም እንኳን በን.ሕ.ቁ. 659/1/ መሠረት አንድ የመድን ውል ተቃራኒ ስምምነት ከሌለ ውጤት መስጠት የሚጀምረው ፖሊሲው ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ ቢሆንም በዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር /2/ መሠረት የመድን ውል ተፈፃሚነቱ የሚጀምረው የመጀመሪያው መደብ አረቦን ሲከፈል ነው ብሎ መዋዋል እንደሚቻል ተመልክቷል፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው መድን ሰጪው እንዲከፈለው ያሰላው አረቦን ወይ ከአንድ ጊዜ በላይ እንዲከፈል ማለትም ተቆራርጦ እንዲከፈል ስምምነት ሲደረግ ወይም ውሉ ፀንቶ ለሚቆይበት ለመጀመሪያው የስምምነት ጊዜ /ዕድሳትን ሳይጨምር/ የሚከፈል አረቦን ሲሆን ነው፡፡

በን.ሕ.ቁ. 659/2/ መሠረት የተፈረመው የመድን ውል ፖሊሲ የመጀመሪያው መደብ አረቦን እስኪከፈል ተፈፃሚነቱን ለማዘግየት መዋዋል አንዳንድ አከራካሪ ውጤቶችን ሊያስከትል እንደሚችል ይገመታል፡፡ ይኸውም በአንድ በኩል የመድኑ ውል ፖሊሲ ተጽፎ ከተፈረመ በኋላ መድን የተገባለት አደጋ ቢደርስ መድን ገቢው መካስ ይገባኛል ብሎ መጠየቅ ይችል ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ሲያስነሳ በሌላ በኩል ደግሞ የመድኑ ውል ፖሊሲ ቢፈረምም ተዋዋዮቹ ተፈፃሚነቱ የሚጀመረው የመጀመሪያ መደብ አረቦን ሲከፈል ነው ብለው በመስማማት የመድን ፖሊሲውን ተፈፃሚነት አግደውታልና አረቦኑ ተከፍሎ እገዳው እስከሚነሳ ድረስ ውሉ ቢመሠረትም በተዋዋይ ወገኖች ላይ ውጤት አይኖረውም ማለት ይቻላል፡፡

በሕግ ረገድ ይህ ዓይነት ስምምነት በሁኔታ መስማማት ነው ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ሲሆን በፍ.ብ.ሕ.ቁ.1871 ላይ እንደተመለከተው አንድ ውል የማቆያ ሁኔታ ተጨምሮበት የተመሠረተ እንደሆነ የውሉ ተዋዋይ ወገኖች ሌላ ተቃራኒ

ሃሳብ ካልገለፁ ውሉ ውጤት ማግኘት የሚጀምረው ማቆያ ሁኔታው ከሚፈፀምበት ቀን ጀምሮ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡ በን.ሕ.ቁ. 659/2/ ሥር ሠፍሮ የሚገኘውም አባባል የማቆያ ሁኔታን የሚመለከት ሆኖ መድን ሰጪውና መድን ተቀባዩ የርሱን ዓይነት ሁኔታ አስገብተው ከተዋዋሉ ውላቸው ሁኔታው እስከሚፈፀም ድረስ ውጤት መስጠት እንደማይጀምር መገንዘብ ቀላል ነው፡፡[3]

በውሉ ምሥረታ ጊዜ በፖሊሲው ላይ ወይም በን.ሕ.ቁ. 657/3/ መሠረት በተሠጠ በጊዜያዊ የመድን ሽፋን ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላይ የመድን ሰጪው ግዴታ ቢጠቀስም የርሱ ግዴታ ተፈፃሚ የሚሆነው በውሉታው ላይ የተመለከተው አደጋ፣ ኃላፊነት ወይም ጊዜ ሲደርስ ብቻ ነው፡፡ የመድንን ውል ልዩ ከሚያደርጉት ጠባዮች አንዱ ውሉ በመድን ተቀባዩ ላይ ከአረቦን ክፍያ አኳያ ወዲያውኑ ተፈፃሚ የመሆኑ ጉዳይ ሲሆን ለመድን ሰጪው ግን ተፈፃሚነቱ የመድን ሰጪውን ኃላፊነት የሚያስቀሩለት ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው በውሉ ላይ የተመለከተው አደጋ ወይም ኃላፊነት ወይም ጊዜ ሲደርስ ብቻ ነው፡፡[4]

ስለዚህ በመድን ሰጪው በኩል በውሉ ምሥረታ ጊዜ የሚፈለግበት ግዴታ ባጠቃላይ አነጋገር የተፈራው አደጋ ሲደርስ ወይም በውሉ የተነገረው ጊዜ ሲሞላ ወይም ኃላፊነት ሲመጣ እክስሃለሁ ብሎ ቃል መግባት ነው ለማለት ሲቻል[5] መድን ገቢው ግን ሌሎች በውሉ ምሥረታ ጊዜ ወይም እንደሁኔታው ከምሥረታው በፊት የሚወድቅበትን ግዴታዎች ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

## የመድን ሰጪውን የአደጋ አስተየየት የሚለውጡበትን ሁኔታዎች /ፍሬ ነገሮች/ መረጃዎች ስለማስታወቅ

ከመድን ውል ልዩ ጠባዮች መካከል አንደኛውና ምናልባትም ዋነኛው ተብሎ ሊጠቀስ የሚገባው ስለፍፁም ቅን ልቡና ጉዳይ ነው፡፡ የመድን ውል በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ቅን ልቦና ላይ በተለይም ደግሞ በመድን ገቢው ፍፁም ቅን ልቦና ላይ የሚመሠረት ውል ነው፡፡

---

[3] አንድን የመድን ውል በን.ሕ.ቁ. 659/1/ ሥር በተገለፀው ዓይነት የማቆያ ሁኔታ አድርጐ መዋዋሉ ግን በተግባር ላይ አንዳንድ ችግሮችን ሊያስነሣ ይችላል፡፡ ጎላ ብሎ የሚታየው የመድን ውል ፖሊሲ ዛሬ ተፈርሞ ውጤት መስጠት የሚጀምረው ግን የመጀመሪያ መደብ አረቦን ሲከፈል ከሆነ የአረቦኑ መከፈል ውሉን ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ ውጤት እንዲሰጥ ያደርገዋል? ወይንስ አረቦኑ ከተከፈለበት ጀምሮ ወደፊት? የሚለውን ጥያቄ ያስከትላል፡፡

[4] Henry vance, Handbook of the Law of Insurance, በተሰኘዉ መጽሐፉ West Publishing Co. (1951) pp. 94-95 የሚከተለዉን አስቀምጧል፡ "A contract of insurance is executory and conditional. It is executory on the part of insured and conditional as regards the insurer."

[5] ይህን ስንል ግን መድን ሰጪው ከሥራው ተግባር የተነሳ ስለተፈራው አደጋ የደረሰው መረጃ ካለ ለመድን ገቢው የማሳወቅ ግዴታ የለበትም ማለት አይደለም፡፡ እ.ኤ.አ. በ1987 ላይና ከዚያም ወዲህ የፍጹም ቅን ልቡና ግዴታ በሁለቱም የመድን ውል ተዋዋዮች ላይ ተፈጻሚ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የመድን ኢንዱስትሪ እጅግ በጣም በዳበረበት በእንግሊዝ አገር ከጥንት ጀምሮ ማለትም እ.ኤ.አ. ከ1766[6] ጀምሮ የመድን ውል የቅን ልቡና ውል መሆኑ የታወቀ ሲሆን በየዘመናቱ ይኸው አስተሳሰብ ሲጠናከር የቆየበት አገር ነው ። አንዱ ታዋቂ የመድን ሕግ ምሁር እንዲህ ይላሉ፦

> The Law Relating to contracts of insurance is part of the general law of contracts. Contracts of insurance are, however, a species of that special class of contract, contracts of utmost good faith. Special rules therefore apply in insurance law relating to non-disclosure and misrepresentation which differ from the rules applicable to contracts generally. Otherwise there is no principle in insurance law which is repugnant to the ordinary principles of the Law of contracts.[7]

*/የመድንን ውል የሚመለከተው ሕግ የጠቅላላ ውል ሕግ አንዱ ክፍል ነው። ሆኖም ግን የመድን ውሎች ልዩ ከሚባሉት የውል ዝርያዎች አንዱ ሆነው "የፍፁም ቅን ልቡና ውሎች" ከሚባለው ክፍል የሚመደቡ ናቸው። በመሆኑም የመድን ውሎችን በሚመለከት ከሌሎች ውሎች በተለየ አኳኋን ተፈፃሚ የሚሆኑ መደበቅን (መሸሸግን) እና ሐሰተኛ መግለጫን የሚመለከቱ ደንቦች አሉ። በተረፈ በመድን ሕግ ውስጥ ከሌሎች ከማናቸውም ተራ የውል መርሆችና ደንቦች ጋር የማይጣጣም መርህ የለም።/*

ትርጉም የፀሐፊው/ ነው።

ሌላ በመድን ሕግ ላይ የጻፉ እንግሊዛዊ ምሁር የሚከተለዉን ያስረዳሉ፦

A Contract of insurance is the primary example of the class of contracts *uberrimae fidei* that is of the utmost good faith. As a result, the parties to it are bound to volunteer to each other before the contract is concluded information which is material to the risk.[8]

*/የመድን ውሉ የፍፁም ቅን ልቡና ተብለው ከሚመደቡት መካከል ዋነኛው ምሣሌ ነው። ከዚህም የተነሣ የውሉ ተዋዋይ ወገኖች ውሉ ከመመሥረቱ በፊት አንዱ ለሌላኛው ለተፈራው አደጋ መረጃ ለመስጠት ይገደዳል*

/ትርጉም የፀሐፊው/ ሲሉ ሌሎችም በርካታ ፀሐፊዎች ስለመድን ውል የፍፁም ቅን ልቡና ውልነት በሰፊው አትተዋል።[9]

---

[6] Carter V Boehm (1766) 3 Burr. 1905.

[7] Raoul Collinvaux, the Law of Insurance 5th ed ,Sweet & Maxwell, London, 1984 p.11

[8] John Birds, Modern Insurance Law, Sweet & Maxwell, London, 1982,p.83

[9] ለምሣሌ፡ E.R. Hardy Ivamy, Principles of Modern Insurance Law 4th ed., Butterworths & Co., (Publishers) Ltd., London, 1986 p. 119 et seq., Merkin and McGee, Insurance Contract Law, Kluwer, London, 1988. (et.passim).

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ የመድን ሕግ መምህር የነበሩት ብሩን ኦቶ ብሪዴም ባጠቃላይ የንግድ ሕጉ ከፍትሐብሔር ሕጉ ጋር ተዛምዶ መታየትና መነበብ እንዳለበት ካወሱ በኋላ ለምሳሌ ያህል ስለመድን ውል ምሥረታ ብለው በመቀጠል የፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1678 በሁሉም ውሎች ላይ ተፈፃሚ ነው:: ለሁሉም ውሎች አስፈላጊ ተብለው በዚህ ቁጥር ሥር ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ውስጥ የችሎታ ጥያቄ የሚዳኘው በፍትሐብሔር ሕግ ነው፣ የፈቃድ ጉዳይም ከሞላ ጐደል እንደዚሁ ሲሆን፣ ነገር ግን የን. ሕ. ቁ. 667 እና 668 ከፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌ የበለጡ ተንኮልንና ስሕተትን የሚመለከቱ ደንቦችን ያስቀምጣሉ በማለት ያስረዳሉ::[10]

የን.ሕ.ቁ. 667 በኢትዮጵያ የመድን ሕግ ውስጥ የቅን ልቡናን ግዴታ በመድን ገቢው ላይ ሲጥል ከዚህም አኳያ ውሉን በሚዋዋልበት ጊዜ ኢንሹራንስ ሰጪው ኃላፊነት የሚወስድባቸውን አደጋዎች ለመመዘን የሚያስችሉትን ማናቸውንም ሁኔታዎች በትክክል መግለጥ አለበት ሲል ይደነግጋል::

ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው ለማለት ባያስደፍርም[11] በመድን ሥራ ሠፊ ልምድ ባላቸው አገሮች እንደሚታመነው በን.ሕ.ቁ. 667 ሥር የተጣሉው ግዴታ መሠረቱ የሚከተለዉ አስተሳሰብ ነዉ:-

> The underwriter knows nothing and the man who comes to him to ask him to insure knows everything, it is the duty of the assured, the man who desires to have a policy, to make a full disclosure to the underwriter without being asked of all the material circumstances, because the underwriter knows nothing and the assured knows everything. That is expressed by saying that it is a contract of utmost good faith *uberrimae fides*[12]

*/መድን ሰጪው የሚያውቀው ምንም ነገር የለም:: መድን እንዲሰጠው ለመጠየቅ የሚመጣው ሰውዬ ግን ሁሉን ነገር ያውቃል፣ በመሆኑም ይህ መድን እንዲሰጠው የሚፈልገው መድን ገቢ አስፈላጊና ጠቃሚ የሆኑትን ሁኔታዎችና መረጃዎች ሳይጠየቅ ለመድን ሰጪው በሙሉ የመግለጽ ግዴታ አለበት:: ምክንያቱም መድን ገቢው ሁሉን ነገር ያውቃል፣ መድን ሰጪው ግን የሚያውቀው ምንም ነገር የለም:: ይህም የመድን ውል የፍጹም ቅን ልቡና ውል ነው:: ፍጹም ቅን ልቡና በሚል አገላለጽ ይጠቃለላል:: /ትርጉም የፀሐፊው/*

---

[10]Brun Otto Bryde. <u>Insurance Law</u>, unpublished, Faculty of Law, Haile Selassie I University, (1983), p.104.

[11] መድን ገቢው የሚያውቃቸውን ወይም ማወቅ ይገባዋል ሊባሉ የሚችሉትን ፍሬነገሮች /facts/ መድን ሰጪውም ሊያውቃቸው ይችላል:: በተለይም ከመድን ሰጪው ሙያ አንፃር ሊያውቃቸው ይገባል የሚባሉት ፍሬነገሮች ቁጥራቸው በርካታ ሲሆን እንደሚችል ይገመታል:: እንደዚሁም ማንም ሰው የሚያውቀውን ፍሬነገር መድን ገቢው አልገለፀም ተብሎ ክርክር ሲቀርብበት አይገባም::

[12] Rozan V Bowen (1982) 32 LIL Rep. 98 at 102

እንግዲህ በን.ሕ.ቁ. 667 ሥር የሠፈረው አባባልም የመጣው መድን ስለሚገባለት ንብረት፣ ሰው ወይም አደጋ የሚያውቀው መድን ጠያቂው ነው ከሚል እምነት ነው ቢባል ስሕተት አይመስለኝም።

በን.ሕ.ቁ. 667 መሠረት መድን ገቢው መግለጽ የሚገባው ሁሉንም መድን የሚጠየቅለትን ንብረት፣ ወይም ሰው፣ ወይም አደጋ የሚመለከቱትንና እርሱ የሚያውቃቸውን ፍሬነገሮች ቢመስልም ነገር ግን መወሰድ ያለበት በመድን ጠያቂው በኩል መገለጽ ያለባቸው ፍሬነገሮች መድን ሰጪው ኃላፊነት እንዲወስድባቸው የሚፈለጉትን አደጋዎች ለመመዘን የሚያስችሉትን ማናቸውንም ፍሬነገሮችን[13] ነው እንጂ ሁሉንም መድን ገቢው የሚያውቃቸውን ፍሬነገሮች አይደለም።

እንደ ኤዉሮፓ አቆጣጠር በ1906 ዓ.ም. በወጣዉ የእንግሊዝ ማሪን ኢንሹራንስ አክት በአንቀጽ 18(2) እና 20(2) መሠረት የአደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ማለት፦ "Any fact which would influence the judgment of a prudent insurer in fixing the premium or determining whether he will take the risk"[14] ነዉ። ይህ በግርድፉ "ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ማለት ማንኛዉም አንድ አመዛዛኝ መድን ሰጪ የሚያስከፍለዉን አረቦን ወይም መድን ሽፋን በመስጠት ሓላፊነትን የሚወስድበትን አደጋ የሚመለከት ፍሬነገር ማለት ነዉ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

በኢትዮጵያ የመድን ሕግ ውስጥ የትኞቹ ፍሬ ነገሮች አስፈላጊና ዋነኛ የአደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮች (material facts) ሊባሉ እንደሚችሉ በግልጽ የተሰጠ ትርጓሜ ወይም ማብራሪያ የለም። የንግድ ሕጉ ሲረቀቅ በነኚህ በን.ሕ. ቁ. 667 እና 668 በስተጀርባ የነበረዉን አስተሳሰብ ፒተር ዊንሺፕ ጠቅለል አድርገዉ እንደሚከተለዉ ይገልጹታል፦

> On the question of facts concealed and false statements, I have included the more nuanced sanctions found in the French law rather than the solutions set out in the Maritime Code, which are perhaps too rigorous.[15]

---

[13] በመሠረቱ አንድ መድን ገቢ መግለጽ የሚጠበቅበት ፍሬነገሮችን (facts material, material facts)እንጂ የመድን ገቢዉን የግል አስተያየት(opinion)አለመሆኑን አንባቢ ልብ ሊል ይገባል። ለአንዳንድ የመድን ዉሎች ምናልባት የመድን ገቢዉ አስተያየት ሊጠየቅ ወይም ሊፈለግ ይችል ይሆናል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ መድን ገቢዉ በሚሞላዉ ፎርም መጨረሻ ላይ የማዉቀዉንና የማምነዉን ያህል በፎርሙ ላይ የሰጠሁት መረጃ ትክክል ነዉ ከማለት በስተቀር ለሰጣቸዉ መረጃዎች ትክክለኝነት ማረጋገጫ ወይም ዋስትና ሊሰጥ አይችልም። በተጨማሪም አንባቢ ከዚህ በታች በግርጌ ማስታወሻ ቁ. 7 ላይ የተጠቀሰዉን መጽሃፍ ከገጽ 98-101 እንደዚሁም ገጽ 104 እና 140ን ይመልከት።

[14] Sections 18(2) and 20(2) of the English Marine Insurance Act of 1906

[15] Peter Winship, (editor and translator) Background Documents of the Ethiopian Commercial Code of 1960, Faculty of Law , Haile Selassie I University, Addis Ababa, 1974 p. 83

የተሸሸጉ እና በትክክል ያልተገለጹ ፍሬነገሮችን ጥያቄ በተመለከተ በባሕር ሕግ ዉስጥ የተካተቱትን ጠበቅ ያሉ መፍትሔዎችን ከመዉሰድ ይልቅ በፈረንሳይ ሕግ ዉስጥ የሚታዩትን ረቀቅ ብለዉ ላላ ያሉትን የማስገደጃ ስልቶችን አካትቻለሁ (ትርጉም የፀሓፊዉ)።

በኢትዮጵያ የባሕር ሕግ ቁጥር 300 ላይ "ስላለመግለጽና አሰተኛ መግለጫ ስለመስጠት" በሚል ሪዕስ የሚከተለዉ ተደንግጓል፦

(1) ኢንሹራንስ የገባዉ ሰዉ ሳይገልጽ መቅረቱ ወይም አሰተኛ የሆነ መግለጫ መስጠቱ ምንም እንኳ በማታለል መንፈስ የተደረገ ባይሆን ለመድረስ በሚያስጉ አደጋዎች (ሪስክ) ላይ ኢንሹራንስ አድራጊዉ ያለዉን አስተያየት የሚቀንሱ ከሆኑ የኢንሹራንሱን ዉል የሚያፈርሱ ናቸዉ።
(2) ሳይገለጽ መቅረቱ ወይም በሃሰት የተሰጠዉ መግለጫ ኢንሹራንስ በተደረገለት ዕቃ ላይ ለደረሰዉ ጉዳት ወይም መጥፋት ምክንያት ሆኖ ባይገኝም እንኳ የኢንሹራንሱን ዉል ፈራሽ ነዉ።
(3) ኢንሹራንስ የተደረገለት ሰዉ የማታለል ሃሳብ አሳይቶ እንደ ሆነ በኢንሹራንስ የተከፈለዉ ዋጋ (ፕሪሚየም) በሞላዉ የማታለል መንፈስ የሌለ እንደሆነ በግማሽ የኢንሹራንስ አድራጊዉ ገንዘብ እንደሆነ ይቀራል።

በእርግጥም በባሕር ሕጉ ላይ የተደነገገዉ ጠበቅ ያለ መመዘኛ ነዉ። መመዘኛዉ ለመድን ሰጪዎች ጥሩ ሊሆን ሲችል ለመድን ገቢዎች ግን ከበድ ያለ ዉጤት ይኖረዋል። የባሕር ሕጉ ድንጋጌ ጠበቅ ያለ ስለመሆኑ በተለይም በእንግሊዝኛ ቅጂ ላይ በግልጽ ይታያል።[16]

ወደ ንግድ ሕጉ ስንመለስ በቁ. 667 ሥር የተመለከተውና "መድን ሰጪው ዋስትና እንዲሰጥባቸው የሚፈለጉትን አደጋዎች ለመመዘን የሚያስችሉትን ማናቸውንም ፍሬነገሮች" የተሰኘው አባባል በኢትዮጵያ ሕግ የማቴሪያሊቲ (ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮች) መለኪያ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

በን.ሕ.ቁ. 668 /1/ ሥር "እውነተኛው ነገር ተገልጾለት ቢሆን ኖሮ ኢንሹራንስ ሰጪው ይህን ውል አይዋዋልም ወይም ተጠቃሚው ከፍ ያለ ገንዘብ እንዲከፍል የሚያደርግበት ውል ይዋዋል ነበር እስከሚያሰኝ ድረስ እነኚህ የተሸሸጉ ነገሮች ወይም በሐሰት የተሰጡ መግለጫዎች የመድን ሰጪውን አስተየየት ለውጠውበት እንደሆነ ነው ..." ተበሎ የገባውም አባባል እንደ ማቴሪያሊቲ መመዘኛ ሊወሰድ ይችላል።

---

[16] Sub-article (1) of Art. 300 of the 1960 Maritime Code of Ethiopia provides: "Any concealment or misrepresentation on the part of the assured, by which the risk insured has been underestimated, shall result in the cancellation of the policy, even in the absence of fraud"

ይህንንም ለማለት የሚያስችለው ተደበቀ ወይም በሐሰት ተገለፀ የሚባለው ፍሬነገር ማንኛውንም መድን ገቢው የመድን ሽፋን እየጠየቀለት ስላለው አደጋ ወይም ሰው ወይም ንብረት የሚያውቀውን ፍሬነገር ሳይሆን የመድን ሰጪውን ያደጋ አስተያየት ሊለውጥበት ይችል የነበረውና የተደበቀው ቢታወቅ ኖሮ ወይም ትክክለኛው ፍሬነገር ቢገለጽ ኖሮ ወይ ለተፈራው አደጋ ዋስትናውን ከመስጠት ይቆጠብ ነበር ወይም ዋስትናውን ለመስጠት ፈቃደኛ እንኳን ቢሆን አስከፍሎ ከተዋዋለው ወይም ሊያስከፍል ከተዋዋለው አረቦን የበለጠ ያስከፍል ወይም ሊያስከፍል ይዋዋል ነበር የሚያሰኝ ሲሆን ነው፡፡

ሌላው መነሣት የሚያስፈልገው ነጥብ በኢትዮጵያ የመድን ሕግ አንድ ፍሬነገር የአደጋ አስተያየት ሊያስለውጥ የሚችል /ማቴሪያል ፋክት/ ነው አይደለም ብሎ ለመወሰን ሕጉ ሥልጣን /መብት/ የሰጠው የመድን ሽፋን እንዲሰጥ ጥያቄ እየቀረበለት ላለው ለዚያው መድን ሰጪ ይመስላል፡፡[17] በሌላ አነጋገር የኢትዮጵያ የመድን ሕግ አንድን የተሸሸገን ወይም በትክክል ያልተገለፀን ፍሬነገር ያደጋ መመዘኛ አስፈላጊ ፍሬነገር ነው አይደለም ለማለት የሚችለው ያው ጥያቄ የቀረበለት መድን ሰጪ እራሱ ነው እንጂ አንድ መድን ሰጪ ተደበቀ የተባለውን ወይም በትክክል አልተገለፀም የተባለውን ፍሬነገር እንደአስፈላጊ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ይወስደዋል ወይንስ አይወስደውም? በሚል ኦብጀክቲቭ መለኪያ እንደማይሄድ ነው ይህንንም የሚያስብለዉ የን.ሕ. ቁ. 667 ድንጋጌ ራሱ ሲሆን የሚለዉም "ዉሉን በሚዋዋልበት ጊዜ ኢንሹራንስ ገቢዉ የሚያዉቃቸዉን ማናቸዉንም ሁኔታዎችና ኢንሹራንስ ሰጪዉ ኃላፊነት የሚወስድባቸዉን አደጋዎች ለማመዛዘን የሚያስችሉትን ማናቸዉንም ሁኔታዎች በትክክል መግለጥ አለበት" ነዉ፡፡ ፍ/ቤቶች ኦብጀክቲቭ መለኪያ እንጠቀማለን ቢሉ እንኳ ይህን ማድረጉ የማይቻልበት ወቅት ነበረ፡፡[18]

ፕሮፌሰር አይቫሚ በእንግሊዝ አገር በሥራ ላይ ያለውን መለኪያ እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

> The test which is usually adopted is whether the non-disclosure of the facts would influence a "prudent" insurer

[17] In a note published in Michigan Law Review, Vol.25 (1927) p. 469, it was stated: "The Insured's non-disclosure (misrepresentation) being material will be assumed to have influenced the insurer to assume the risk, to have induced him to enter into a contract which he would otherwise have declined or to take a less premium then he would otherwise have demanded."

[18]ከ 1967 እስከ 1983 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ መድን ሰጪ ብቻ (የኢትዮጵያ መድን ድርጅት) በነበረበት ሁናቴ ፍርድ ቤቶች አንድ reasonable insurer ተደበቀ የተባለውን ወይም በትክክል አልተገለፀም የተባለውን ፍሬነገር እንደአስፈላጊ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ያየዋል አያየውም? የሚለውን ለማጣራት /theoretically and fictitiously/ ካልሆነ በስተቀር ይችሉ እንዳልነበረ ግለጽ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በተቻለ መጠን ፍርድ ቤቶች ኦብጀክቲብ መለኪያ ወደመጠቀም ቢያዘነብሉ የተሻለ ነው የሚል ግምት አለ፡፡

(though in some cases the term "reasonable" has been substituted for "prudent") Another test is whether a "reasonable" assured would consider them material…In no case is it relevant to consider whether the non- disclosure would influence the particular insured concerned or whether the assured himself sought that the facts were material.[19]

ምንም እንኳን አንዳንዴ "አመዛዛኝ" የሚለውን ቃል ቢጠቀሙበትም ብዙ ጊዜ የሚወሰደው መለኪያ /መመዘኛ/ መደበቁ የአንድን "ጠንቃቃ" መድን ሰጪ ያደጋ አስተያየት ይነካ ወይም ያሰቀይር እንደሆነ ነው፡፡ ሌላኛው መለኪያ ደግሞ አንድ "አመዛዛኝ" መድን ገቢ የተደበቁትን ፍሬነገሮች እንደ ማቴሪያል ይወስዳቸው እንደሆነ ሲሆን … መቼውንም ቢሆን የተደበቀው ፍሬነገር የመድን ሽፋን እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበለት የተለየውን መድን ሰጪ ውሳኔ ይነካል ወይም ያስቀይረዋል ብሎ መውሰድ አግባብነት የለውም፡፡ መድን ገቢውም ራሱ በግሉ የተደበቁት ፍሬነገሮች ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮች ናቸው ወይስ አይደሉም ይበል ተብሎም አይወሰድም/ ትርጉም የፀሐፊው ነው፡፡

ሌላው በኛ ሕግ ውስጥ በግልጽ ያልተመለከተው በን.ሕ.ቁ. 667 ሥር የተጣለበትን ግዴታ መወጣት ያለበት መድን ገቢ የትኞቹ ፍሬነገሮች ያደጋ መመዘኛ ናቸው ብሎ ማለት ያለበት እርሱ ነው ወይንስ መድን ሰጪው ወይንስ ሁለቱም ናቸው የሚለው ጥያቄ ሲሆን ይህም አከራካሪ ሊሆን እንደሚችል መገንዘቡ መልካም ነው፡፡

መድን ገቢው በን.ሕ.ቁ. 667 ላይ የተጣለበትን ግዴታ ሳይወጣ ሲቀር ምን ውጤት እንደሚከተል በን.ሕ.ቁ. 668 ላይ ተመልክቶአል፡፡ በዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር /1/ ሥር ተጽፎ እንደምናነበው መድን ገቢው "ሆን ብሎ"[20] የመድን ሰጪውን የአደጋ አስተያየት ሊለውጥበት የሚችል ፍሬነገር /ማቴሪያል ፋክት/ ደብቆ ከተገኘና የተደበቀው ፍሬነገር ቢገለጽ ኖሮ ወይም በትክክል ተገልጾ ቢሆን ኖሮ መድን ሰጪው ወይ የመድን ዋስትናውን የመስጠት ግዴታ ውስጥ አይገባም ነበር ወይም ዋስትናውን ለመስጠት ፈቃደኛ እንኳን ቢሆን አስከፍሎ ከተዋዋለው አረቦን በላይ ያስከፍል ነበር ወይም ሊያስከፍል ከተዋዋለው በላይ ለማስከፈል ይዋዋል ነበር የሚያሰኝ ከሆነ ውሉ ፍርስ እንደሚሆንና መድን ሰጪውም የተቀበለውን አረቦን እንደሚያስቀር ተደንግጓል፡፡

---

[19] Ivamy፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9፣ ገጽ 126 ፡፡

[20] ሕጉ "እያወቀ" ነው የሚለው፡፡ ይህ አባባል ግን በሕጉ ላይ ከተመለከተው ውጤት አኳያ ሲታይ ብዙም ትክክል አይመስልም፡፡ ሆን ብሎ የሚያውቁትን ነገር መደበቅ ወይም በሐሰት መግለጽ ግን fraud /ተንኮል/ ያለበት መሆኑን ያመለክታል፡፡

በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 637/81 በይግባኝ ባይ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና በመልስ ሰጭ በወ/ሮ አዳነሽ አድማሱ (የእነ መሠረት ከተማ ሞግዚት) መካከል በተደረገዉ ክርክር ሟች የመልስ ሰጭ ባለቤት አቶ ከተማ ገ/መስቀል ለሞት የሕይወት መድን ዋስትና ሲገዙ በሞሉት መግለጫ ላይ የጉበት በሽታ የለብኝም ብለዉ ሞልተዉ በጉበት ሕመም ሕወታቸዉ ካለፈ በኋላ መድን ሰጪዉ ሟቹ የጉበት ሕመም እንዳለባቸዉ እያወቁና ለዚህ ህመም ህክምና እየተደረገላቸዉ መሆኑን እያወቁ በሞሉት መግለጫ ላይ የጉበት በሽታ የለብኝም ማለታቸዉ የመድን ሰጪዉን የአደጋ አስተያየት ሊያስለዉጥ የሚችል እዉነት መደበቅ ስለሆነ ከሃላፊነት ነጻ እንደሚያደርገዉ ተከራክሮ ረትቶበታል፡፡ በዚህ መዝገብ ላይ በዋናነት ክርክር የተካሄደዉ መድን ሰጪዉ ዉሉ ፍርስ ስለሆነ ሓላፊነት የለብኝም የሚለዉን ክርክር ሟች መድን ገቢ በሕይወት እያሉ ሊያነሳ ይችል እንደሆን እንጂ የመድን ገቢ ሕይወት ካለፈ በኋላ ማንሳት አይችልም የሚል ክርክር እንደነበረ አንባቢያን ማወቃቸዉ መልካም ነዉ፡፡[21] በተመሳሳይ መልኩ በ1994 ዓ.ም. በከሳሽ በአቶ አዲሱ ተመስገን እና በተጠሪ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት መካከል በግልግል ዳኝነት ጉባዔ ፊት ተካሂዶ በነበረዉ ክርክር ይኸዉ ሀሰተኛ መግለጫ የመስጠት ጭብጥ ተነስቶ የግልግል ዳኝነት ጉባዔዉ ጉዳዩን በአምስት ፓራግራፎች እንደሚከተለዉ ገልጾታል፡-[22]

> አንድ መድን ገቢ የመድን ዉል በሚዋዋልበት ጊዜ የፍጹም ቅን ልቦናን (utmost good faith) መሠረት በማድረግ ዋስትና እንዲገባለት ለተጠየቀዉ ንብረት የሚያዉቀዉን ሁሉ ተጠይቆም አስጠይቆም መግለጽ እንደሚጠበቅበት የንግድ ሕግ ቁጥር 667 ይደነግጋል፡፡
>
> በንግድ ሕግ ቁጥር 668(1) መሠረት የመድን ዉል የገባዉ ሰዉ እያወቀ እዉነተኛውን ነገር የሸሸገ ወይም የሃሰት መግለጫ የሰጠ እንደሆነ እዉነተኛው ነገር ተገልጾለት ቢሆን ኖሮ ኢንሹራንስ ሰጪው ይህን ዉል አይዋዋልም ወይም ከፍ ያለ አረቦን አስከፍሎ ይዋዋል ነበር እስከሚያሰኝ ድረስ እነዚህ የተሸሸጉ ነገሮች ወይም በሃሰት የተሰጡ መግለጫዎች የኢንሹራንስ ሰጪውን የአደጋ አሰተያየት ለዉጠዉበት እንደሆነ ዉሉ ፍርስ ነዉ፡፡ እንደ እንግሊዝኛው ቅጂ “the policy shall be of no effect” ኢንሹራንስ ሰጪውም ተከፈለዉን አረቦን ያስቀራል፡፡
>
> ከሳሽ ዋሰትና ለተገባላቸዉ ማሽኖች መግዣ የተሰጠ ብድር በሰጣቸዉ በኢትዮጵያ ልማት ባንክ አማካይነት እ.አ.አ 01/05/93 እና እ.አ.አ 13/2/96 በተጻፈ የመድን መግቢያ መጠየቂያ ቅጽ ላይ የማሽኖች ዋጋ ብር

---

[21] በ1989 ዓ.ም በ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጥናት ምርምርና ሕትመት መምሪያ ታትሞ ወጥቶ የነበረዉን የፍርዶች መጽሐፍ ቮልዩም አንድ ከገጽ 49-51 ይመልከቱ፡፡

[22] የኢትዮጵያ አርቢትሬሽን ኤንድ ኮንሲሊዬሽን ሴንተር <u>የግልግል ዳኝነት ዉሳኔዎች</u>፣ ፩ኛ መጽሐፍ፣ገጽ 195 እና 196፡፡ከላይ ከተመለከቱት ሁለት ዉሳኔዎች በተጨማሪ አንባቢያን የአዲስ አበባ ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 84/89፣02188 የሰጣቸዉን ዉሳኔዎች እንደዚሁም ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ድሬደዋ ምድብ ችሎት በፍ/መ/ቁ 01798 የሰጠዉን ዉሳኔ መመልከት ይችላሉ

92,820 (ዘጠና ሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሃያ ብር) እና ብር 282,705 (ሁለት መቶ ሰማንያ ሁለት ሺህ ሰባት መቶ አምስት ብር) መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚህ በኋላ በአደጋ ወቅትም ቢሆን ማሽኖቹ አዲስ የተገዙ ናቸዉ በማለት ከሃግቤስና ጄኔራል መርካንታይል ከተባሉ ኩባንያዎች ደረሰኞች አቅርበዋል። ከነዚህ ሁኔታዎች የምንረዳዉ ከሳሹ ዋስትና እንዲገባላቸዉ የጠየቁላቸዉ ማሽኖች አዲስ ናቸዉ በማለት የመድን መግቢያ ጥያቄ ማቅረባቸዉን ነዉ። ለዚህ ክርክር ምክንያት የሆነዉ አደጋ ከደረሰ በኋላ ተከሳሽ ድርጅት ጉዳቱን አስመልክቶ ተገቢዉን ምርመራ (ሰርቬይ) ለማድረግ በቦታዉ የተገኘ ሲሆን በምርመራዉ ወቅት የተገኘዉ ሪፖርት እንደሚያመለክተዉ ማሽኖቹ በፍጹም አዲስ አይደሉም። ይህም ሁኔታ አጠራጥሮት ከሳሹ ድርጅት ደረሰኝ ካቀረበባቸዉ ከሃግቤስና ጄኔራል መርካንታይል ኩባንያዎች ዕቃዎቹን አስመልክቶ ለሺያጩ መረጃ ሲጠይቅ ሁለቱም ኩባንያዎች ያረጋገጡት ማሽኖቹ ለከሳሹ አለመሸጣቸዉንናቀረቡ የተባሉት ደረሰኞችም በነርሱ በኩል ያልተዘጋጁ መሆናቸዉን ነዉ። ስለሆነም ከሳሹ አሮጌዎችን አዲስ የተገዙ በማስመሰል ዋስትና ገብተዋል። በዚህ ሁኔታ መድን ሰጪዉን የአደጋዉን ግምት አሳስተዉበታል። ይህም ድርጊታቸዉ ከላይ በጠቀስነዉ የንግድ ሕግ ቁጥር 667 መሠረት የሚጠበቅባቸዉን የፍጹም ቅን ልቦና ተጻራሪ ነዉ። ይህ ከላይ የተገለጸዉ የፍጹም ቅን ልቦና መርህ በመድን ገቢዎች ተጥሶ እዉነተኛዉ ነገር የተሸሸገ ወይም ሃሰት መግለጫ የተሰጠ እንደሆነ መድን ሰጪዉም እዉነቱን ቢያዉቅ ኖሮ አይዋዋልም ወይም ከፍ ያለ አረቦን ሊያስከፍል ይችላል የሚያስብል በመሆኑና ከሳሹ የሰጡት መግለጫ የመድን ሰጪዉን የአደጋ አስተያየት የለወጠበት በመሆኑ ከሳሽ ከተከሳሽ ጋር አለኝ የሚሉት የመድን ዉል በንግድ ሕግ ቁጥር 668 ንኡስ ቁጥር 1 መሠረት ፍርስ ነዉ። በመሆኑም ተከሳሽ ለደረሰዉ አደጋ በመድን ሕግ መሠረት ኃላፊነት የለበትም።

በመሆኑም በንግድ ሕግ ቁጥር 668(1) መሠረት የመድን ዉሉ ፍርስ (of no effect) ስለሆነና እንዲህ ዓይነት ዉሎች በተለየ ሁኔታ ከመጀመሪያዉ (ከመመስረታቸዉ) ጀምሮ ዉጤት የሌላቸዉ ወይም እንዳልተቋቋሙ የሚቆተሩ ናቸዉ። ስለዚህ የመድን ዉሉ ፍርስ ስለሆነ ከሳሽ የሚጠይቁት ካሳ የለም።

የን.ሕ.ቁ. 668/1/ የእንግሊዝ ቅጂ "It shall be of no effect" ነው የሚለው ይህ አባባል ደግሞ "ፍርስ ነው" ከሚለው የበለጠ ጠበቅ ያለ ይመስላል። በእንግሊዝኛው ቅጂ ከተሄደ የተደበቀ ወይም በሐሰት የተገለጸ ፍሬነገር ኖሮ ሁኔታው በን.ሕ.ቁ. 668/1/ እንደሚሸፈን ከተረጋገጠ በመድን ገቢውና በመድን ሰጪው መካከል

የተመሠረተው ውል ምንም ውጤት እንደሌለው ነው የሚናገረው፡፡[23] በቁጥር 668/1/ የአማርኛው ቅጂ አባባል ከተሄደ ውሉ ይፈርሳል፡፡ /"ፍርስ ነው" የሚለው አባባል "ይፈርሳል" ከሚለው የተለየ ትርጉም ይሰጣል ካልተባለ/ ውሉ የሚፈርስ ከሆነ ደግሞ ተዋዋይ ወገኖች በተቻለ መጠን ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ቦታ የመመለሳቸውን ውጤት ያስከትላል፡፡[24] ምናልባት "It shall be of no effect" የሚለው አባባል "Void ab initio"ከሚለው የላቲን አባባል ጋር ይመሳሰል ይሆናል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ውሉ በሕግ ፊት ጨርሶ እንዳልኖረ፣ እንዳልተመሠረተ ይቆጠራል ያሰኛል፡፡

በሌላ በኩል ግን "ፍርስ ነው" ቢባል ወይም "ይፈርሳል" ወይም "ፈራሽ" ነው ቢባል ምንም ልዩነት አያመጣም ሊባል ይቻል ይሆናል፡፡ ውጤቱ ዞሮ ዞሮ በተቻለ መጠን ተዋዋይ ወገኖችን ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ቦታ የመመለስ ሲሆን ከውሉ ሊመነጩ ይችሉ የነበሩት ግዴታና መብቶች አይመነጩም ማለት ነው ተብሎ ሊወሰድም ይቻላል፡፡[25] ሆኖም ግን በን.ሕ.ቁ 668/1/ ሥር የተመለከተውን ልዩ የሚያደርገው ሌላው ሁኔታ መደበቁ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ መስጠቱ ሆን ተብሎ መደረጉ ሲረጋገጥና ከዚህም የተነሣ ውሉ ፍርስ ሲሆን ተዋዋይ ወገኖች በተቻለ መጠን ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ መመለሳቸው መቅረትና መድን ሰጪውም የተቀበለውን አረቦን ማስቀረቱ ነው፡፡[26]
የመድን ሰጪው የተቀበለውን አረቦን ማስቀረት ራሱ ተዋዋይ ወገኖች ዉሉ ፍርስ ነዉ ሲባል ከዉሉ ምስረታ በፊት ወደ ነበሩበት ያለመመለሳቸዉን ያሳያል፡፡

ምናልባት አረቦኑ እንዳይመለስ የተከለከለው መድን ገቢው ከፈጸመው ማታለል የተነሳ በመድን ሰጪው ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለማካካስ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚያውም አታላዩን በገንዘብ ለመቅጣትም ሳይሆን አይቀርም፡፡ ይህ ድርጊት

---

[23] በአማርኛ የፍትሐብሔር እና የንግድ ህጎቻችን ዉስጥ አገልግሎት ላይ ዉለዉ የምናነባቸዉ አንዳንድ ቃላት በህጎቹ የእንግሊዝኛ ቅጂ ዉስጥ ከሚሰጡት መልዕክት የተለዩ መሆናቸዉን አንባቢያን ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ ለምሳሌ በእንግሊዝኛዉ ቅጂዎች "void" "voidable" ተብለዉ ልዩነት ባለዉ መልኩ ሲቀመጡ በአማርኛ ቅጂዎች ላይ ግን ልዩነቶቹ ብዙም ግልጽ አይደሉም፡፡ እንደዚሁ በእንግሊዝኛዉ ቅጂዎች ዉስጥ "invalidation" እና "cancellation" ተለይተዉ ሲቀመጡ በአማርኛ ቅጂዎች ላይ ግን በሁለቱ መካከል ልዩነት እንደሌለ ተደርጎ ተጽፏል፡፡ ሌሎች ተጨማሪ ምሳሌዎችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

[24] የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1815፡፡

[25] በሕግ ፊት እንዳልተመሠረቱ እንዳልኖሩ የሚቆጠሩ 'Void ab initio" የተሰኙ ውሎች ምናልባት unenforceable ስለሆኑ በፍርድ ቤት እንዲፈርሱና ተዋዋይ ወገኖች በተቻለ መጠን ከውሉ በፊት ወደ ነበረበት ቦታ ይመለሱ ለማለትም አይቻልም ይሆናል፡፡

[26] በዚህ ጽሑፍ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 4 ላይ እንደተገለፀው አንድ የመድን ውል በመድን ገቢው ላይ ወዲያውኑ ተፈጻሚ ሲሆን በመድን ሰጪው ላይ ውጤት የሚኖረው ግን የተፈራው አደጋ ወይም ጊዜ ሲደርስ ወዘተ ስለሆነ በውሉ ምሥረታ ጊዜ ወይም ከዚያ በኋላ ለመድን ገቢው ተሰጥቶት መድን ገቢው ውሉ በመፍረሱ ምክንያት የሚመልሰው ነገር የለውም፡፡

በወንጀልም ያስቀጣል::[27] መድን ሰጪው አረቦን ማስቀረት ብቻ ሳይሆን በን.ሕ. ቁ. 668 ሥር የሰፈረዉ ሁኔታ ሲያጋጥም በወንጀልም ሊያስቀጣ ይችላል::

የመድን ገቢው ሆን ብሎ ሐሰተኛ መግለጫ መስጠት ወይም መሸሸግ መድን የተገባለት አደጋ ከመድረሱ በፊት ወይም በኋላ ቢታወቅ የተለያየ ውጤት ስለማስከተሉ በን.ሕ.ቁ. 668/1/ ላይ የተመለከተ ነገር የለም:: ሕጉ በዚህ ረገድ ፀጥ ቢልም ሆን ብሎ መሸሸጉ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ መስጠቱ መድን የተገባለት አደጋ ከደረሰ በኋላ ቢታወቅ በቁ. 668/1/ የተመለከተውን ውጤት አያስከትልም ብሎ መገመቱ በአንድ በኩል የዋህነት ሲሆን በሌላ በኩል ሕጉ ሊጠብቀው የፈለገውን (public policy) ዝቅ ማድረግ ነዉ:: ስለሆነም ያንድ መድን ገቢ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮችን ሆን ብሎ ደብቆ መገኘት ወይም ሆን ብሎ በሐሰት መግለጽ የተደረሰበት ተፈርቶ መድን የተገባለት አደጋ ከመድረሱ በፊት ይሁን በኋላ ምንም ለውጥ አያመጣም:: ውጤቱም ያው በን.ሕ.ቁ.668/1/ ሥር የተጻፈውና ከዚህ በላይ ያየነው ይሆናል::

መድን ገቢው ያደጋ መመዘኛ ሊሆኑ የሚችሉትን ፍሬነገሮች የደበቀው ወይም በሐሰት የገለጸው ሆን ብሎ በተንኮል መድን ሰጪውን ለማሳሳት ካልሆነ ውጤቱ በን.ሕ.ቁ. 668/1/ ሥር ከተመለከተው የተለየ ነው:: ውጤቶቹ በን.ሕ.ቁ. 668/2/ /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተጻፉት ይሆኑና በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር ከተመለከተው ለዘብ ያሉ ሆነው እናገኛቸዋለን:: የንዑስ ቁጥር /2/ አነጋገር ራሱ ቁልጭ አድርጐ እንደሚያመለክተው ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም እንኳን መሸሸጉ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ መስጠቱ ሆን ተብሎ ያልተደረገ ከሆነና መድን ሰጪውም ሆን ተብሎ መደረጉን ማስረዳት ካልቻለ ውሉ አይፈርስም::

የን.ሕ.ቁ. 668/2/ አነጋገር ሁለት ዋና ዋና ነጥቦችን ይዟል:: 1ኛ/ለውሉ ፍርስ መሆን ወይም አለመሆን መለኪያው መሸሸጉ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ መስጠቱ ሆን ተብሎ መደረጉ ወይም አለመደረጉ መሆኑን፣እና 2ኛ/መደበቁ ወይም በሐሰት መገለጹ ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑን ማስረዳት ያለበት መድን ሰጪው መሆኑን ነው::

---

[27] ሆን ተብሎ በራስ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ከመድን ውል ነገር በተያያዘ የማጭበርበርና የተንኮል ሥራ በ1949 ዓ.ም. ሥራ ላይ በነበረዉ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 659 መሠረት ያስቀጣ ነበር:: በ1997ዓ.ም. በወጣዉ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 698(1) ላይ ደግሞ **እንሹራንስ በሚመለከት የሚፈፀም የአታላይነት ድርጊት** በሚል ርዕስ እንደሚከተለዉ ተደንግጓል::
" ማንም ሰዉ የማይገባ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ-
ሀ/ኢንሹራንስ የተገባበት አደጋ በመፍጠር፣ ወይም
ለ/በዉሉ ዉስጥ በተገለፀዉ ጥቅም ላይ ተጽዕኖ በሚያደርግ አኳኋን ኢንሹራንሱን ገንዘብ ልክ የዉሉን ዘመን ወይም የኢንሹራንሱ ተጠቃሚዎችን በሚመለከት ፍሬነገር በመደበቅ፣ በማሳሳት፣በማረጋገጥ፣ወይም ይህንኑ በሚመለከት ሀሰተኛ መግለጫ በመስጠት አንድ የኢንሹራንስ ማሕበርን ያታለለ እንደሆነ……በቀላል እሥራት ወይም ሁኔታዎቹ በይበልጥ ከባድ ሲሆኑ ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና ከብር ሃምሳ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል….::


Law Library
versity

ለውሉ “ፍርስ” መሆን ወይም አለመሆን የተሰኘውን አባባል ትንሽ ማየት ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም፣ ምክንያቱም የን.ሕ.ቁ.668 ንዑስ ቁጥር/2/ “ውሉ አይፈርስም” የሚል አነጋገር ነው የተጠቀመው። በሌላ በኩል በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር ያለው አባባል ግን “ፍርስ ነው” የሚል ነው። በቁ. 668 ንዑስ ቁጥር /2/ የተመለከተዉ በሕግ ጣልቃ ገብነት ዉሉ “ፍርስ” ወይም “of no effect” አለመሆኑን ለማመልከት ይመስላል። በመሆኑም “ውሉ አይፈርስም” ከሚለው አነጋገር የበለጠ የሕግ አውጪውን ፍላጐት ሊገልጽ ይችል የነበረው “ውሉ ፍርስ አይሆንም” የሚለውን አባባል ቢጠቀምበት ኖሮ ነበር ቢባል ስሕተት አይመስለኝም።

የን.ሕ.ቁ. 668/2/ “ውሉ አይፈርስም” ወይም በእንግሊዝኛው አነጋገር “ውሉ ፀንቶ ይቆያል” ይበል እንጂ ውሉ ሊቋረጥ እንደሚችል በዚሁ ንዑስ ቁጥር ሥር በ/ሀ/ ላይ ተመልክቶአል። ይህም የሚያሳየው በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል እስከሚቋረጥበት ጊዜ ድረስ በሕግ ፊት የፀና ውል እንደኖረ የሚያስረዳ ሆኖ ሐሰተኛ መግለጫ መስጠቱ ወይም የተደበቀ የአደጋ መመዘኛ ፍሬነገር መኖሩ ተደርሶበት ውሉን መድን ሰጪው ለማቋረጥ ወስኖ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ እስካቋረጠበት ጊዜ ድረስ ውለታው ውጤት እንደሚኖረው ነው። ለምሳሌ ያህል አንድ ሰው ተሽከርካሪውን ለግጭት አደጋ በ 2002 ዓ.ም. መጀመሪያ በመስከረም ወር ላይ ለብር 120.000 ለአንድ ዓመት መድን ቢያስገባና በኅዳር ወር በዚያው ዓመት በተሽከርካሪው ላይ ትንሽ የግጭት ጉዳት ደርሶበት መድን ሰጪው 5000 ብር ያህል ቢከፍለውና በሚያዝያ ወር 2002 ዓ.ም. ውስጥ ሆን ተብሎ ሳይሆን በስሕተት የተሸሸገ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር እንደነበር ቢደረስበትና መድን ሰጪው ከዚህ የተነሳ ውሉን ለማቋረጥ ወስኖ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ቢያቋርጥ የውሉ መቋረጥ የሁለቱን የወደፊት ግንኙነት ከፍጻሜ ያደርሰዋል እንጂ ወደኋላ ተመልሶ <u>በኅዳር ወር</u> 2002 ዓ.ም. የተከፈለውን የ5000 ብር ካሣ አይነካም። በዚህ ምሣሌ ሥር የተነሳው የመሸሸግ ጉዳይ በን.ሕ.ቁ. 668/1/ ሥር የሚወድቅ ቢሆን ኖሮ ግን ውሉ ራሱ ፍርስ ስለሆነና በሕግ በፊት እንዳልተደረገ ወይም እንደውጤት አልባ ውል ስለሚቆጠር መድን ሰጪው በኅዳር ወር 2002 ውስጥ የከፈለውን ብር 5000 መልሶ መጠየቅ እንደሚችል ይገመታል።

ሌላኛው በን.ሕ.ቁ. 668/2/ /ሀ/ ሥር የተጠቀሰው ነጥብ መድን ሰጪው በውለታው መቀጠል ከፈለገ ማለትም ማቋረጡን ካልፈለገ ሆን ተብሎ ሳይሆን በስሕተት የተሸሸገውን ወይም በሐሰት የተገለጸው የአደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ባይደበቅ ኖሮ ወይም በትክክል ቢገለጽ ኖሮ ያስከፍል ወይም ሊያስከፍል ይዋዋል የነበረውን አረቦን አስልቶ ከዚሁ ላይ መድን ገቢው የከፈለውን ወይም ሊከፍል የተዋዋለውን ቀንሶ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት አስከፍሎ ምናልባትም ኪሣራውን ጨምሮ በማስከፈል ውሉን ሊቀጥል እንደሚችል ነው።

በን.ሕ.ቁ. 668/2/ /ለ/ ሥር እንደተመለከተው ሆን ተብሎ ሳይሆን በስሕተት የተደበቀው ወይም በሐሰት የተገለፀው የአደጋ መመዘኛ ፍሬ ነገር መኖሩ የታወቀው መድን የተገባለት አደጋ ከደረሰ በኋላ የሆነ እንደሆነ ውጤቱ ለመድን

ገቢው መጥፎ አይደለም፡፡ በሌላ ሌላ ምክንያት መድን ሰጪው ከሃላፊነት ይድን እንደሆነ እንጂ በዚህ ንዑስ ቁጥር ሥር በሚወድቅ መሸሸግ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ መስጠት መድን ሰጪው ከመካስ ሃላፊነት ነፃ እንደማይሆን ስለተደነገገ መደረግ ያለበት የተደበቀው ቢታወቅ ኖሮ ወይም በሐሰት የተገለጸው በትክክል ቢገለጽ ኖሮ መድን ሰጪው ለአደጋው ሽፋን ያስከፍል ወይም ሊያስከፍል ይዋዋል በነበረውና ባስከፈለው ወይም ሊያስከፍል በተዋዋለው መካከል ያለውን ልዩነት መድን ሰጪው ለመድን ገቢው ከሚከፍለው ገንዘብ ላይ ይቀንሰዋል፡፡

ከዚህ በላይ ስለመደበቅና ሐሰተኛ መግለጫ መስጠት ሕግ የሚለውን ለማየት ተሞክሯል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በኢትዮጵያ አንጋፋዉ፣ ዋናዉና ትልቁ መድን ሰጪ የሆነዉ ኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች አንፃር መሸሸግና ሐሰተኛ መግለጫ መስጠት እንዴት ይታያል? የሚለውን ጥያቄ ባጭሩ እናያለን፡፡ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች ከእንግሊዝ አገር መድን ሰጪዎች እንደተወሰዱ ሁሉ ሌሎች በኢትዮጵያ ዉስጥ ያሉት መድን ሰጪ ኩባንያዎች የሚጠቀሙባቸውን ፖሊሲዎች የወሰዱት ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት ነዉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ጽሁፍ ዉስጥ የተካተቱት አንጋፋዉ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምባቸውን ፖሊሲዎች የሚመለከቱ አስተያየቶች ሌሎች መድን ኩባንያዎች ለተመሳሳይ አደጋዎች ለሚጠቀሙባቸዉ ፖሊሲዎች ያገለግላሉ፡፡

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት በሚጠቀምበትና አሁን በሥራ ላይ ባለው የሠራተኞች የካሳ ፖሊሲ /workmen's compensation policy/ ላይ 'ሁኔታዎች' "conditions" በሚለው ክፍል ሥር በ10ኛው ቁጥር ላይ ማንኛውም የአደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ቢደበቅ ወይም በሐሰት ቢገለጽ በደፈናው ፖሊሲው ውድቅ እንደሚሆን ከመጸፉ በስተቀር በን.ሕ.ቁ. 668 ላይ እንደተመለከተው ሆን ተብሎ ሲደረግና በስሕተት ወይም ባለማወቅ ሲደረግ የተለያዩ ውጤቶች እንደሚያስከትል አልተገለፀም፡፡

በቤቶችና በሌሎች ነገሮች በኃይል ሠብሮ የመግባት ፖሊሲ (Burglary & Housebreaking policy) ላይ አሁንም ሁኔታዎች (conditions) በሚለው ክፍል ሥር በ2ኛው ቁጥር ላይ የመድን ገቢው በማመልከቻ ላይ የሞላቸው መግለጫዎች እውነት መሆን መድን ሰጪው በፖሊሲው መሠረት በኃላፊነት ለመጠየቅ እንደቅድመ ሁኔታ ተደርጐ እንደሚወሰድና መድን ገቢው በማመልከቻው ውስጥ ካሠፈራቸው መግለጫዎች ሐሰተኛ የሆነ ካለ ወይም ሳይገለጽ የቀረ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር /ማቴሪያል ፋክት/ ከተገኘ ፖሊሲው ውድቅ ይሆናል ይላል፡፡ ይህም አባባል በንግድ ሕጉ በን.ሕ.ቁ. 668 ሥር ከሠፈረው የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ምናልባት በን.ሕ.ቁ. 668/1/ ሥር ከተመለከተው ጋር ሊመሳሰል ይቃጣው ይሆናል፡፡ ነገር ግን በቁ. 668/1/ ሥር የተመለከተው ጠንከር ያለ ውጤት እንዲመጣ መድን ገቢው ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮችን የደበቀው ወይም በሐሰት የገለፀው ሆን ብሎ መሆን እንዳለበት ስንመለከት በዚህ በያዝነው በቤቶችና በኃይል ሰብሮ የመግባት ፖሊሲ /Burglary and Housebreaking policy / ላይ ግን ሆን ተብሎ ይሆን በቸልተኝነት ይሁን

ወይም በስሕተት ሳይለይ በደፈናው ብቻ መድን ገቢው ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮችን ሳይገልጽ መቅረቱ ወይም በሐሰት መግለጹ ፖሊሲውን ውድቅ እንደሚያደርገው መጻፉን እንረዳለን።

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለእሳትና ለመብረቅ አደጋ መድን በሚጠቀምበት ፖሊሲ /Fire and Lightning policy/ ውስጥም 'ሁኔታዎች' conditions በሚለው ክፍል በአንደኛው ቁጥር ላይ ያደጋ መመዘኛ መረጃዎችን ያለመግለጽ ወይም በሐሰት መግለጽ በደፈናው የመድን ሰጪውን በፖሊሲው መሠረት ለመካስ መጠየቅን እንደሚያስቀርለት ሲያመለክት በግል ተሽከርካሪ ለ3ኛ ወገን ኃላፊነት ፖሊሲ /Private Vehicle third party policy/ ላይም አሁንም 'ሁኔታዎች' conditions በሚለው ክፍል በመጀመሪያ ቁጥር ላይ የመግለጫዎች እውነትነት ለመድን ሰጪው በፖሊሲው መጠየቅ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ተመልክቷል። በንግድ ተሽከርካሪዎች ፖሊሲም ላይ ይኸው ሠፍሮ ይገኛል።

በፊደሊቲ ጋራንቲ /Fidelity Guarantee/ ፖሊሲ ላይ ደግሞ በመድን ገቢው የተሰጡት መግለጫዎች ውሉ የቆመበት ዋነኛ መሠረት basis of the contract ተብለው እንደሚወሰዱ ሲነበብ በአካል ጉዳት መድን ፖሊሲ ላይም ያልተገለፀ ወይም በሐሰት የተሠጠ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ካለ በደፈናው ፖሊሲው ውድቅ እንደሚሆን ተጽፎ ይገኛል።

አሁን በሥራ ላይ ካሉት የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች መካከል ወደ ን.ሕ.ቁ. 668 ቀረብ ተደርገው የተቀረጹት፡- የሕይወት መድን ፖሊሲ፣ የሁሉም ዓይነት አደጋ ፖሊሲ /all risks policy/ እና የገንዘብ ፖሊሲ /Money policy/ የሚባሉት ብቻ ናቸው ቢባል ስሕተት አይመስለኝም። ይህንንም ያልኩበት ዋናው ምክንያት በነዚህ ሶስት ፖሊሲዎች ላይ በተመለከተው መሠረት ውሉ ውድቅ የሚሆነው መድን ገቢው ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮችን ሆን ብሎ ካልገለፀ ወይም ሆን ብሎ ሐሰተኛ መግለጫዎችን ከሰጠ ብቻ ነው ስለሚል ነው።

ባጠቃላይ ሕጉና አብዛኞቹ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮች ከመደበቅና በሐሰት ከመግለጽ አኳያ ብዙም ተጣጥመው አናገኛቸውም። አብዛኛዎቹ ፖሊሲዎች የመድን ገቢውን መብት የሚያጣብቡ ሆነው እናገኛቸዋለን። ምናልባት ይህ ችግር የመጣው በኮንቲኔንታል የሕግ ሲስተም (Continental Legal System) ለተቀረፀ የመድን ሕግ የኮመንሎው (Common Law) ፖሊስዎችን ከመጠቀም ሳይሆን አይቀርም። የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች የእንግሊዝ መድን ሰጪዎች የሚጠቀሙባቸው ፖሊሲዎች ሳይሆኑ አልቀሩም።

በመጨረሻም በ የኮመንሎው ሲስተም (Common Law System) አገሮች ማለትም በሁለቱ የዚህ ሲስተም ተጠቃሽ አገሮች በዩናትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካና በእንግሊዝ አገር ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮች ሆን ተብሎ ቢደበቁ ወይም በሐሰት ቢገለፁ ወይም በስሕተት ቢደበቁ ውጤቱ አንድ ነው። መድን ሰጪው ፖሊሲውን

ውድቅ ነው ሊል ይችላል። በአሜሪካ አገር ባንዳንድ አካባቢዎች የሚከተለዉ አስተሳሰብ ይንፀባረቃል፡-

> The material representation must be fraudulently made in order to avoid the policy. The defendant must show not only that the representation was material and false in fact, but that it was willfully and knowingly made form a fraudulent or corrupt motive or with intent to deceive.[28]

*/ፖሊሲውን ውድቅ ነው ለማሰኘት ያደጋ መመዘኛው ሐሰተኛ መግለጫ በተንኮል የተደረገ መሆን አለበት። ይህም በመሆኑ ተከሳሹ ማረጋገጥ ያለበት የተሰጠው ፍሬነገር ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር መሆኑንና ይኸውም በሐሰት የተሰጠ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የተሰጠው ሐሰተኛ መግለጫ መሆኑ እየታወቀ ሆን ተብሎ በተንኮልና በማሳሳት ፍላጐት  የተሰጠ መሆኑም ጭምር መሆን ይኖርበታል/* ትርጉም የፀሐፊው። ከላይ የተመለከተዉ አስተሳሰብ እንደተጠበቀ ሆኖ በአሜሪካ አገር በሠፊው ሥራ ላይ ያለውና ሥር የሰደደው ሕግ የሚከተለዉ ነዉ፡-

> … That a false representation if it be a fact material to the risk avoids the policy irrespective of the good faith of the one who makes it. A false statement or declaration of fact material to the risk and upon which the policy is based, will avoid the policy, whether that misrepresentation be the result of intention or mistake not so made.[29]

*/ያደጋ መመዘኛ የሆነ ሐሰተኛ መግለጫ፣ መግለጫ ሰጪው በቅን ልቡና ይስጥ አይስጥ ፖሊሲውን ውድቅ ያደርገዋል። እንደፖሊስው መሠረት ተደርጐ በሚወሰድ ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገር ላይ የተደረገ ሐሰተኛ መግለጫ ለመሰጠቱ መንስኤው ስሕተት ይሁን ወይም በቅን ልቡና የተደረገ ይሁን ወይም ሆነ ተብሎ መደረጉ እግምት ውስጥ ሳይገባ ፖሊሲውን ውድቅ ያደርገዋል/።* /ትርጉም የፀሐፊው ነው/ የተሰኘው ነው።

በእንግሊዝ አገር እንኳንስ ሆን ተብሎ ታስቦ መድን ሰጪውን ለማሳሳት የተደረገ *መሸሸግ ወይም ሐሰተኛ መግለጫ* ቀርቶ An innocent misrepresentation affords the party misled a ground for avoiding the policy, a rule which also applies in the case of non-disclosure.[30] *በቅን ልቡና የተሰጠ ሐሰተኛ መግለጫ በመግለጫው ምክንያት ለተሳሳተው ወገን ፖሊሲውን ውድቅ ማድረጊያ ምክንያት ይሰጠዋል። ይህ ደንብ በመሸሸግም ላይ ተፈጻሚ ነው።* ተብሎ ተወስዷል።

Law Library
A. A. University
[illegible] Addis Ababa
Ethiopia

---

[28] Michigan Law Review , supra note 17, p.468

[29] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ.28 የተመለከተዉ።

[30] Raoul Collinvaux, ግርጌ ማስታወሻ ቁ.7 ገጽ 99

## አደጋ እየከበደ መሄዱን ስለመግለጽ

ይህ ንዑስ ርዕስ ከዚህ በታች ባለዉ ክፍል ዉስጥ ሊታይ የሚችል ሲሆን እዚህ እንዲመጣ የተደረገዉ ከመሸሸግ እና ሃሰተኛ መግለጫ ከመስጠት ጋር ስለሚያያዝ መሆኑን ለአንባቢያን መግለጽ እወዳለሁ፡፡

አደጋ እየከበደ መሄዱን ወደማስታወቅ ግዴታ ስንመለስ በን.ሕ.ቁ.667 ላይ ውሉ ሲመሠረት ወይም ከውሉ ምሥረታ በፊት መድን ገቢው ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮችን መግለጽ እንዳለበት ግዴታ ሲጥል ውል ከተመሠረተ በኋላ ደግሞ አደጋው እየከበደ ስለመሄዱ የመግለጽ ግዴታን በን.ሕ.ቁ. 669 ሥር ተመልክቶ እናገኛለን፡፡

የን.ሕ.ቁ. 669 ከርሱ በፊት ከተጻፉት ከቁጥር 667 እና 668 ተከታይ ሆኖ ከውለታው ምሥረታ በኋላም ቢሆን የፍጹም ቅን ልቡና አስፈላጊነት የጎላ መሆኑን የሚያሳውቅ ቁጥር ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮች በትክክልና ሳይደበቁ ተገልጸው መድን ሰጪው ኃላፊነት ስለሚወስድበት አደጋ በትክክልና በሚገባ ተረድቶ ተገቢውን አረቦን በማስከፈል ወይም ለማስከፈል በመዋዋል አንድ የካሳ መድን ፖሊሲ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረ በኋላ መድን የተገባለት ንብረት ውሉ ሲመሠረት ለተፈራው አደጋ ተጋልጦ ከነበረው የበለጠ ቢጋለጥ የተፈራውና መድን የተገባለት አደጋ እየከበደ መሄዱን እንገነዘባለን፡፡ ይህም ተፈርቶ መድን የተገባለት አደጋ የመድረሱን ዕድል probability እየጨመረው መሄዱን ይጠቁምና ውሉ ሲመሠረት ወይም ከመመሥረቱ ቀደም ብሎ መድን ሰጭው እግምት ውስጥ ያላስገባቸው አዳዲስ ክስተቶች መኖራቸውን ያሳያል፡፡ ሕጉም በዚህ ረገድ መድን ገቢው አዳዲስ የተከሠቱትን የመድን ሰጪውን የአደጋ አስተያየት ሊለውጡበት የሚችሉትን ፍሬነገሮች ለመድን ሰጪው ማስታወቅ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

በን.ሕ.ቁ.669 ሥር ሕጉ ማንኛውም ዓይነት መድን የተገባለት አደጋ እየከበደ መሄዱን የሚያሳዩ ሁኔታዎች እንዲገለጹ ግዴታ አልጣለም፡፡ ይልቁንም ሕጉ መድን ገቢው እንዲገልፀው የፈለገው ያደጋው እየከበደ መሄድ ደረጃውና መጠኑ መድን ሰጪው ላደጋው ሽፋን ለመስጠት ውል ሲያደርግ እንዲህ እየከበደ መሄዱን ቢያውቅ ኖሮ ያደጋውን ኃላፊነት ለመቀበል አይዋዋልም ነበር ወይም ቢዋዋልም እንኳን ካስከፈለው ወይም ሊያስከፍል ከተዋዋለው አረቦን የበለጠ አስከፍሎ ይዋዋል ነበር ሲያሰኝ ነው፡፡

በሌላ አነጋገር ከውሉ ምሥረታ በኋላ የተከሠተውን የአደጋ ክብደት ወደኋላ መልሶ ይህ በኋላ የተፈጠረውና የታወቀው ማክበጃ ሁኔታ ውሉ ሲመሠረት ቢታወቅ ኖሮ መድን ሰጪው ወይ ጨርሶ አልዋዋልም ይል ነበር ወይም ለመዋዋል ፈቃደኛ እንኳን ቢሆን በምንም ዓይነት አስከፍሎ የተዋዋለውን ወይም

ሲያስከፍል ለተዋዋለው አነስተኛ አረቦን አይዋዋልም ነበር ሲያሰኝ ነው ማለት ነው::

በን.ሕ.ቁ. 669 ሥር እንደተደነገገዉ በተመሳሳይ መልኩ በኢትዮጵያ የባህር ሕግ ቁ. 301 "ይደርሳል ተብሎ የሚያሰጋዉ አደጋ ስለ መክበዱ" በሚል ርዕስ የሚከተለዉ ተደንግጓል፦

(1) የኢንሹራንስ ዉል በሚፀናበት ጊዜ ይደርሳል ተብሎ የሚያሰጋዉ አደጋ የከበደ እንደሆነ ይህንኑ ሁኔታ እንዳወቀ ለኢንሹራንስ አድራጊዉ ካላስታወቀ የኢንሹራንስ ዉሉ ፈራሽ ይሆናል።

(2) ይህ የአደጋዉ መክበድ ለኢንሹራንስ አድራጊ የተነገረዉ እንደሆነና ይህም የአደጋ መክበድ የደረሰዉ ኢንሹራንስ በገባዉ ሰዉ ምክንያት የሆነ እንደሆነ የኢንሹራንሱ ገንዘብ ለርሱ ቀሪ ሆኖ ወዲያዉኑ ዉሉን መሻር ወይም የኢንሹራንሱ ገንዘብ እንዲጨመር ለማስገደድ ይችላል:: አደጋዉ የከበደዉ በሌላ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ግን ገንዘቡን በመጨመር ኢንሹራንሱ ይቀጥላል::[31]

ባንፃሩ በእንግሊዝ አገር ያደጋ እየከበደ መሄድ ለተዋዋይ ወገኖች ስምምነት የተተወ ጉዳይ ነዉ:: ተዋዋይ ወገኖች በዉለታቸዉ ዉስጥ መድን ገቢዉ ያደጋዉን እየከበደ መሄድ ለመድን ሰጪዉ የማሳወቅ ግዴታ እንዳለበት ካላስገቡ በስተቀር መድን ሰጪዉ ኃላፊነት የወሰደበት አደጋ እየከበደም እንኳ ቢሄድ መድን ገቢዉ ሁኔታዉን ማሳወቅ አይጠበቅበትም::

በእንግሊዝ አገር ባጠቃላይ አነጋገር ያደጋ መመዘኛ ፍሬ ነገሮችን የማሳወቅ ግዴታ ከቅድመ ዉል ምስረታ ጋር እና ከዉል እድሳት ጋር የተያያዘ ነዉ:: ይህንንም ጆን በርድስ እና ኖርማ ሄርድ እንደሚከተለዉ ያስቀምጡታል፦

> The duty to disclose material facts is cast upon the proposer or insured before the contract or a renewal is concluded. At common law, there is no general duty to disclose material facts that occur when they occur during the period of insurance.[32]

ሆኖም በእንግሊዝ አገር ግዴታዉ በህግ በመድን ገቢዎች ላይ የተጣለ አይሁን እንጂ በዉሎች ዉስጥ ግዴታዉን አስገብቶ መዋዋል ግን አልተከለከለም:: በአንዳንድ የመድን ዉሎች በተለይም ለእሳት አደጋ ለሚገቡ የመድኖች ዉሎች የተፈቀደ ነዉ:: ጆን በርድስ እና ኖርማ ሄርድ እንደሚከተለዉ ያብራራሉ፦

> Certain contracts of insurance, though most notably those of fire insurance do, in practice, impose a duty on the insured to disclose facts occurring during the insurance which materially increase the risk. The term that

---

[31] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት <u>የባሕር ሕግ</u>፣ነጋሪት ጋዜጣ ቁ. ፩፣ በ1952 ዓ.ም. በተለይ የወጣ፣ አዲስ አበባ

[32] John Birds and Norma Hird, <u>Modern Insurance Law</u> , (5th ed.), Sweet & Maxwell, London, 2001, p.122.

imposes such a duty is usually, though not necessarily, a promissory warranty, since it provides that upon a failure to disclose, the insurer can avoid the policy.[33]

ጆን በርድስ እና ኖርማ ሄርድ እንደጻፉት በዉል የሚጣለዉ ያደጋን እየከበደ መሄድ የማሳወቅ ግዴታ መድን ገቢዉን የሚያስገድደዉ በቋሚነት ወይም በዘላቂነት የመድን ሰጪዉን ያደጋ ሃላፊነት የሚያከብዱ ፍሬ ነገሮችን በሚመለከት እንጂ ለጊዜዉ ብቻ ወይም አንዳንዴ የሚያከብዱትን አይደለም። መድን ገቢዉ ለጊዜዉ ብቻ ወይም አንዳንዴ የሚያከብዱትን እንዲገልጽ አይገደድም።[34]

ከመድን ውል ምሥረታ በኋላ አደጋው እየከበደ መሄዱን የማስታወቅ ግዴታ ብቻ ሳይሆን በን.ሕ.ቁ. 669/1/ ላይ የተጣለው የመክበዱ መንስዔ ዓይነትና መድን ገቢው በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለበትም ተመልክቷል። በዚሁ መሠረት ለአደጋው እየከበ መሄድ ምክንያቱ ወይም መንስኤው የመድን ገቢው የራሱ ድርጊት ከሆነ ይህ አደጋ አክባጅ ድርጊት ወይም ሁኔታ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ መረጃው ለመድን ሰጪው መነገር አለበት። ለአደጋው እየከበደ መሄድ ምክንያቱ ወይም መንስኤው የመድን ገቢው ድርጊት ሳይሆን ሌላ ከሆነ መድን ገቢው የአደጋ አክባጅ ሁኔታ መከሰቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ አሥራ አምስት ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ለመድን ሰጪው ማስታወቅ እንዳለበት ሕጉ ግዴታ ሲጥል ይህንን የ15 ቀናት የጊዜ ገደብ በውሉ ላይ አርዝሞ መዋዋል በግልጽ ባይከለክልም ቀንሶ መዋዋልን ግን የን.ሕ.ቁ.669/1/ ይከለክላል።

በን.ሕ.ቁ. 669/1/ የተመለከተዉን የማስታወቅ ግዴታና የጊዜ ገደብ ሁኔታን በምሣሌ ለማየት ብንሞክር፣ ለምሣሌ አንድ ሰው ለውሃ ማመላለሻ የሚጠቀምበት ቦቴ መኪና ኖሮት መኪናውን ለእሳት አደጋ መድን አስገብቶ ሳለ የመኪናውን አገልግሎት ከውሃ ማመላለሻነት ወደ ነዳጅ ማመላለሻነት ቢቀይረው ጥሩ የአደጋ መክበድ ሁኔታ ስለሚሆንና መድን ሰጪው ውሉ ሲመሠረት ይህን ቢያውቅ ኖሮ አልዋዋልም እንኳን ባይል አስከፍሎ ከተዋዋለው ወይም ሊያስከፍል ከተዋዋለው አረቦን የበለጠ ያስከፍል ነበር ወይም ሊያስከፍል ይዋዋል ነበር ስለሚያሰኝ መድን ገቢው የውሀ ማመላለሻ ቦቴ መኪናውን ወደ ነዳጅ ማመላለሻነት ከቀየረበት ቀን አንስቶ በ15 ቀን ውስጥ ሁኔታውን ለመድን ሰጪው መግለጽ እንዳለበት እንረዳለን። በሌላ በኩል ግን ይኸው መድን የተገባለት መኪና በውሃ አመላላሽነት ወደ ጦር ግምባር ተልኮ ለተወሰነ ጊዜ አገልግሎት ሲሰጥ ከቆየ በኋላ መድን ገቢው ለአደጋው እየከበደ መሄድ መንስዔ ወይም ምክንያት ባለመሆኑ /ራትኑ የመኪናው ወደ ጦር ግምባር መላክ የአደጋ መክበድ ሆኖ የሚቆጠር ከሆነና ይህንኑ አስታውቆ ከሆነ/ መድን ገቢው ስለአደጋው መክበድ ማስታወቅ

[33] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ.32 የተመለከተዉ ከገጽ 122-123።

[34] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁ.32 የተመለከተዉ ገጽ 123።

የሚፈስግበት በውሃ አመላላሽነት ወደ ጦር ግምባር የተላከው ቡቴ መኪናው ወደ ነደጅ ማመላለሻነት መቀየሩን ካወቀበት ቀን ጀምሮ አሥራ አምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይሆናል።

መድን የተገባለት አደጋ እየከበደ መሄዱን ማስታወቅና አለማስታወቅ ምን ምን ውጤት እንደሚያስከትል በን.ሕ.ቁ. 669/2/ እና /3/ ሥር ተጽፎአል። ስለሆነም ውጤቶቹ ሶስት ናቸው እነርሱም 1ኛ/ በን.ሕ.ቁ. 668/1/ ሥር በተገፈው ሁኔታ ውሉ ፍርስ ሊሆን እንደሚችል፣ 2ኛ/ በመድን ሰጪው ፍላጎትና ምርጫ ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል፣እና 3ኛ/ እየቀጠለ የሄደውን አደጋ ገምግሞ መድን ሰጪው ተገቢውን ተጨማሪ አረቦን በማስከፈል ውሉን እንዲቀጥል ማድረግ እንደሚችል ነው።[35]

የአደጋን እየከበደ መሄድ መግለጽ የን.ሕ.ቁ 669/1/ የመድን ገቢው ግዴታ አድርጐ ያስቀምጠው እንጂ በፖሊሲዎች ላይ አልተመለከተም። ቀደም ሲል በጨረፍታ እንደጠቀስኩት ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች በቀጥታ የተወሰዱት ከእንግሊዝ አገር መድን ሰጪዎች ስለሆነ ሳይሆን እንደማይቀር ሲገመት በእንግሊዝ አገር እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ማለትም እ.ኤ.አ. እስከ 1985[36] ዓ.ም. ድረስ የፍጹም ቅን ልቡናን ግዴታ በውሉ ምሥረታ ጊዜ ብቻ መወጣት እንደሚያስፈልግና ከውሉ ምሥረታ በኂላ ስለአደጋው እየከበደ መሄድ መግለጽ አስፈላጊ እንዳልነበረ መገንዘቡ መልካም ነው።

በን.ሕ.ቁ. 669/4/ ሥር እንደተመለከተው የአደጋን እየከበደ መሄድ የማስታወቅ ግዴታና ውጤቶች በሕይወት መድን ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን ተደንግጐአል። የሕይወት መድንን በሚመለከቱ የንግድ ሕጉ ቁጥሮች አካባቢም የተባለ ነገር የለም። በሌላ በኩል በሕይወት መድን ፖሊሲ ላይ ጠቅላላ ግዴታዎች በሚለው ክፍል ሥር መድን የገባው ድርጅቱ በጽሑፍ ሳይፈቅድለት በወታደራዊ፣ በባሕር ኃይል ... ወይም ማናቸውንም ይበልጥ አደጋ የሚያስከትል ሥራ ቢይዝ ወይም ... ሥራ ላይ ቢሠማራና ከላይ በተጠቀሱት በማናቸውም ምክንያቶች ቢሞት በዚህ ውል መሠረት የድርጅቱ ግዴታ ይኸው ይበልጥ አደገኛ የሆነው ሥራ ታውቆ ቢሆን ኖሮ የተከፈለው አረቦን ሊገዛ የሚችለውን የዋስትና ገንዘብ መክፈል ይሆናል። ይኸውም ይበልጥ አደገኛ የሆነው ሥራ ዋስትና ሊሰጠው የማይችል ከሆነ የድርጅቱ ግዴታ ለውሉ የተከፈለውን ጠቅላላ አረቦን /ተጨማሪ አረቦን ሳይጨምር/ መመለስ ይሆናል ይላል።

---

[35] በን.ሕ.ቁ. 669/1/ሥር የተጣለው ግዴታ የሚያስከትለውን ዝርዝር ውጤት አንባቢው ከዚህ በላይ ከገጽ 7 እስከ 26 ያደጋ መመዘኛ ፍሬነገሮችን ስላለመግለጽ ወይም በሐሰት ስለመግለጽና የሚያስከትለውን ውጤት በሚመለከት የተገፈውን እንዲመለከቱ ፀሐፊው ይጠቁማል።

[36] The Litsion Pride (1985) 1 LLoyd's Rep. 437

**ውሉ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ /መድን የተገባለት አደጋ ከመድረሱ በፊት ወይም በውሉ የተመለከተው ጊዜ ከመሙላት በፊት/ የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ**

**የአረቦን አከፋፈል**[37]

በዚሁ ጽሁፍ ዉስጥ ቀደም ሲል ለማመልከት እንደተሞከረው ምንም እንኳን የኢንሹራንስ /የመድን/ መግቢያ ገንዘብ /አረቦን/ አከፋፈል በተዋዋይ ወገኖች ውል የሚወሰን ቢሆንም አንድ የመድን ውል ፖሊሲ ተፈርሞም ፖሊሲው ዉጤት መስጠት የሚጀምረው ግን የመጀመሪያው መደብ ኘሪሚዩም ሲከፈል ነው ብሎ መዋዋል እንደሚቻል በን.ሕ.ቁ. 659/2/ ተደንግጓል፡፡ ይህ የን.ሕ.ቁ. 659/2/ ድንጋጌ ለተወሰነ ጊዜ ፖሊሲውን የሚያስኬደው አረቦን ተከፍሎ ከዚያ ያ የተወሰነው ጊዜ ካለቀ በኂላ ማደሻ ኘሪሚዩም ስለማስከፈል ይሁን ወይም ለተወሰነ ጊዜ የተገባ ፖሊሲ ኖሮ ለዚያ ለተወሰነ ጊዜ ከሚከፈለው ኘሪሚዩም ላይ የሆነ ያህል እንደ መጀመሪያው መደብ የሚቆጠር ካልከፈሉ ፖሊሲው ውጤት መስጠት እንደማይጀምር ይናገር ተለይቶ አልታወቀም፡፡

ስለ አረቦን አከፋፈል መድን ድርጅት በሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች ላይ ምን እንደተባለ ከዚህ በታች ባጭሩ ለማየት እንሞክራለን፡፡

በሠራተኞች የካሣ መድን ፖሊሲ /workmen's compensation policy/ ላይ 'ሁኔታዎች' conditions በሚለው ክፍል በ6ኛው ቁጥር ላይ "የመጀመሪያው መደብ" አረቦንና "ማሳደሻ አረቦን" የሚሉ ሐረጎች እናገኛለን፡፡ "የመጀመሪያው መደብ" ማለት ውሉ ለአንድ ዓመት ተገብቶ ከሆነ ለዚያ ለአንድ ዓመት የሚውል ሙሉ አረቦን የሚል ስሜት ያለው ሲመስል አንድ ዓመት ሲያልቅ የሚከፈለው አረቦን ደግሞ "ማሳደሻ" አረቦን ይሆናል፡፡

በሁሉም አደጋ መድን ፖሊሲ /All risks Policy/ ላይም እንደተመለከተው "የመጀመሪያ መደብ" አረቦን "first premium" የተሰኘው አባባል ውሉ ፀንቶ ለሚቆይበት ጊዜ የሚከፈለውን አረቦን እንደሚመለከት ስንረዳ ከሕይወት መድን አኳያ ስንመለከት ግን ለአንድ ዓመት የሚከፈለው አረቦን ተከፋፍሎ በ Installment ሊከፈል ስለሚችል "first premium" የመጀመሪያው መደብ አረቦን ማለትም ፖሊሲው ለአንድ ዓመት ተገብቶ ከሆነ ለዚያ ዓመት የሚከፈለው ሙሉ አረቦን ላይሆን ይችላል፡፡ "የመጀመሪያው አረቦን" በዚህ ረገድ የመጀመሪያው Installment ተደርጐ ሊወሰድ እንደሚችልና በን.ሕ.ቁ. 659/2/ መሠረትም ምንም እንኳን ፖሊሲው ቢፈረምም ይኸው የመጀመሪያው Installment ኘሪሚየም ካልተከፈለ

---

[37] ይህ ፀሃፊ በኢትዮጵያ ጠበቆች የሕግ መጽሔት በመግቂ 1ቁ.1 ላይ ያሳተመዉን ይመልከቱ፣ እንደዚሁም በጥጋቡ አንበርበር እና በኢትዮጵያ መድን ድርጅት መካከል ስለ አረቦን መከፈልና ስለመድን ዉል መታደስ በነበረዉ ክርክር ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ በፍ/ቤቱ የፍርዶች መጽሄፍ ቅጽ ፩ ከገጽ 121-126 ይመልከቱ

ፖሊሲው ዉጤት መስጠት አይጀምርም የሚል ስምምነት ማድረግ እንደሚቻል እንገነዘባለን።

መድን ድርጅት በሚጠቀምባቸው ሌሎች ፖሊሲዎች ላይ ሠፍሮ የሚገኘው መድን ሰጪው ለመስጠት እየተዋዋለ ስላለው የመድን ሽፋን መድን ገቢው አረቦን ለመክፈል መስማማቱን የሚገልጽ ሲሆን ውሉ ሲመሠረት መድን ገቢው አረቦኑን ውሉ ፀንቶ ለሚቆየበት ጊዜ ባንዴ ይክፈል ወይም ከፋፍሎ ይክፈል ባያመለክትም ባንዴ ከፍሎ እንደሚዋዋል ይገመታል። ቢሆንም ግን ተዋዋይ ወገኖች የአረቦኑን አከፋፈል በሚመለከት እንደፈለጉ ሊዋዋሉ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም።

ዋነኛው በዚህ በያዝነው "የአረቦን አከፋፈል" በተሰኘው ንዑስ ርዕስ ሥር ለማንሳት የፈለግሁት በን.ሕ.ቁ.666 እና 709 ላይ የተመለከተዉ አረቦን በጊዜ ካልተከፈለ ምን ውጤት እንደሚያስከትል የተደነገጉትንና በፖሊሲዎች ላይ ስለአረቦን ክፍያ የሠፈሩትን በሚመለከት አንዳንድ ሐሳቦችን ነው።

ምንም እንኳን በን.ሕ.ቁ.666/1/ መሠረት መድን ገቢው ለኢንሹራንስ መግቢያ የሚከፈለውን ገንዘብ በውሉ ላይ በተወሰነው ቀን መክፈል ግዴታው መሆኑ ቢደነገግም መድን ገቢው አረቦኑን በውሉ በተወሰነው ጊዜ ባለመክፈሉ ብቻ ውሉን ማፍረስ እንደማይቻል በን.ሕ.ቁ. 666/2/ ላይ ተመልክቷል። የንዑስ ቁጥር /2/ ክልከላ ተፈጻሚነቱ ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም ባይኖርም ሲሆን የዚህን ንዑስ ቁጥር ድንጋጌ ዋና መልዕክት አረቦን በውሉ ላይ በተመለከተው ጊዜ ካልተከፈለ ውሉ ፈራሽ ነው በሚል ሰበብ ስምምነቱን ወደጎን ማድረግ እንደማይቻል ነው። የንግድ ሕጉ ሲረቀቅ በዚህ በንግድ በን.ሕ.ቁ. 666 በስተጀርባ የነበረዉን አስተሳሰብ ፒተር ዊንሺፕ እንደሚከተለዉ ይገልጹታል፦

> As for the payment of the premium, in order to spare the insured from the sudden unforeseen rupture of the contract, I have included a provision, as has been done in the French law, requiring a mandatory waiting period of one month during which the insurance is only suspended. The provision is a matter of public policy and cannot be varied by the parties.[38]

*የአረቦን አከፋፈልን በተመለከተ መድን ገቢዉ ለድንገተኛ የዉል መቋረጥ እንዳይጋለጥ ለመከላከል በፈረንሳይ ሕግ ዉስጥ እንዳለዉ ዓይነት ለአንድ ወር ጊዜ ዉሉ ታግዶ የሚቆይበትን በግዴታ የመጠበቂያ ጊዜን የሚመለከት ድንጋጌ አስገብቻለሁ(ትርጉም የፀሃፊዉ)*

አረቦኑ በፖሊሲው ላይ በተመለከተው ጊዜ ካልተከፈለ ውሉ ለተገባበት ጊዜ ሙሉውን ፀንቶ ይቆያል ማለት አይደለም። የን.ሕ.ቁ.666/2/ አባባል ግልጽ እንደሚያደርገው መድን ሰጪው አረቦኑ በፖሊሲው ላይ በተመለከተው የመክፈያ

---

[38] Peter Winship, (editor and translator) Background Documents of the Ethiopian Commercial Code of 1960, Faculty of Law , Haile Selassie I University, Addis Ababa, 1974 p. 82

ጊዜ ባለመከፈሉ ውሉ በዚሁ ምክንያት ብቻ ወዲያውኑ /automatically/ ፈራሽ ነው ሊል አይችልም፡፡ በን.ሕ.ቁ. 666/3/ እና /4/ እንደዚሁ በራሱ በንዑስ ቁጥር /2/ መሠረት መድን ሰጪው ያልተከፈለው አረቦን እንዲከፈለው ጥያቄ ማቅረብ እንዳለበትና እንዲከፈለው በጠየቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከተከፈለው ውሉታው ይቀጥላል ካልተከፈለው ግን በን.ሕ.ቁ. 666/2/ ሥር የተጻፈው"... ባለመከፈሉ ብቻ ውሉን ለማፍረስ አይቻልም" የሚለው አባባል የተወዘፈው አረቦን ባይከፈልም ውሉ ተዋዋይ ወገኖች ፀንቶ እንዲቆይ ለተዋዋሉት ጊዜ ይፀናል ማለት አለመሆኑን ማጤን ያስፈልጋል፡፡

በን.ሕ.ቁ.666/3/ ላይ በቁጥር የአንድ ወር ጊዜ ተሰጠ እንጂ ሃሳቡ በፍትሐብሔሩ ሕግ የጠቅላላ ውል ሕግ ክፍል ውስጥ በቁጥር 1772 ላይ የተመለከተውን ማስጠንቀቅን ወይም ደግሞ በቁጥር 1770 ሥር የተጻፈውን የችሮታ ጊዜን[39] የሚመለከት ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ልዩነቱ ማስጠንቀቂያ ተባለ የችሮታ ጊዜ በን.ሕ.ቁ. 666/3/ ሥር የመለከተውን የሰጠው ሕግ ነው እንጂ ተዋዋዩ መድን ሰጪ አለመሆኑ ነው፡፡

ወደ ን.ሕ.ቁ. 666/3/ አባባል ስንመለስ መድን ሰጪው አረቦን እንዲከፈለው ከጠየቀበት ቀን አንሥቶ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ካልተከፈለው ውሉ እንደሚታገድ እናነባለን፡፡ የውሉ መታገድ ምን እንደሆነ፣ ምን ውጤት እንደሚያስከትል በሕጉ ላይ የተሰጠ ምንም ዐይነት ማብራሪያ ባይኖርም በዚህ ንዑስ ቁጥር ሥር "ውሉ ይታገዳል" የሚለው አባባል ምን እንደሆነና ምንስ ውጤት እንደሚያስከትል ባጭሩም ቢሆን ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

ስለውሉ መታገድና ስለውጤቱ ከማውሳታችን በፊት መድን ሰጪው የተወዘፈው አረቦን እንዲከፈለው ጥያቄ ካደረገበት[40] ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ወር ጊዜ ድረስ ውሉ እንደፀና እንደሚቆይ መገንዘቡ መልካም ነዉ፡፡ የአረቦን ክፍያ ጥያቄ በመድን ሰጪው ከተደረገበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መድን የተገባለት አደጋ ቢደርስ መድን ሰጪው የመካስ ግዴታ እንደሚወድቅበትም መረዳቱ አስፈላጊ ነው፡፡ የተወዘፈው አረቦን እንዲከፈለው ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መድን የተገባለት አደጋ ቢደርስ መድን ሰጪው መከፈል ይገባ የነበረውን አረቦን ከካሣው ላይ ቀንሶ ለመድን ገቢው መስጠት እንደሚችል ይገመታል፡፡ ምናልባትም ኪሣራም ሊጠይቅ ይችል ይሆናል፡፡

---

[39] የኢትዮጵያ መድን ድርጅት "የፋታ ጊዜ" ይለዋል፡፡

[40] በን.ሕ.ቁ. 666/3/ ላይ ያለው የአንድ ወር ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የመድን ሰጪው የውዝፍ አረቦን ክፍያ ጥያቄ ከተላከበት ቀን /ጊዜ/ ጀምሮ ነው? ወይንስ ጥያቄው ለመድን ገቢው ከደረሰበት ጊዜ /ቀን/ ጀምሮ ነው? የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ከውል ድርድር ማለትም hoffer እና acceptance አንፃር እንደሚታወቀው Dispatch theory እና Reception theory የሚባሉ ንድፈ ሐሳቦች አሉ፡፡ የን.ሕ.ቁ. 666/3/ አባባልም ከነኚህ ባንዱ ሥር መሸፈን አለበት ሊባል ይቻላል፡፡

በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር አርባ ላይ እንደተመለከተው ያንድ ወር ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የመድን ሰጪው የዉዝፍ አረቦን ጥያቄ ከተላከበት ቀን አንስቶ ይሁን ወይም ጥያቄው ለመድን ገቢው ከደረሰበት ቀን አንስቶ የሚለው አከራካሪ ጥያቄ እንደተጠበቀ ሆኖ መድን ሰጪው ጥያቄ ካቀረበ ከአንድ ወር በኋላ ውሉ እንደሚታገድ በን.ሕ.ቁ. 666(3) ተደንግጉአል፡፡ "ይታገዳል" የሚለው ቃል ውሉ "ይፈርሳል" እንዳልሆነ በን.ሕ.ቁ. 666 ንዑስ ቁጥር (4) ሥር ከተጻፈው መረዳት ይቻላል፡፡ "ይታገዳል" ማለት "ይፈርሳል" ካልሆነ ሊኖረው የሚችለው ትርጉም ለጊዜው ተፈጻሚነቱ ይቆማል ማለት ነው፡፡ በተለይም የእንግሊዝኛውን ቅጂ ስናይ "suspended" ስለሚልና ይህ ማለት ደግሞ "ለጊዜው የመቆም"፣ "ለጊዜው የመታገድን" "ለጊዜው የመወገድን" ስሜት ስለሚሰጥ የን.ሕ.ቁ. 666/3/ ትርጉም በመድን ሰጪውና በመድን ገቢው መካከል የተደረገው ውለታ ሳይፈርስ ወይም ሳይቋረጥ ለጊዜው ውሉ በተዋዋይ ወገኖች ላይ ተፈጻሚነቱ ወይም ውጤታማነቱ ይቆማል ወይም ይቆያል ማለት ነው፡፡ ባጭሩ በን.ሕ.ቁ. 666/3/ ሥር ሕግ አውጪው ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት መድን ሰጪው አረቦኑ እንዲከፈለው ከጠየቀበት ቀን አንስቶ ሳይከፈለው አንድ ወር ካለፈ ከዚያ በኋላ መድን የተገባለት አደጋ ቢደርስ ማለትም የእገዳው ጊዜ ከተጀመረ በኋላ ለሚደርሰው አደጋ መድን ሰጪው ሊክስ እንደማይገደድ ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው በን.ሕ.ቁ. 666/3/ ሥር የተጻፈው የእገዳ ጊዜ ውሉን ለጊዜው ተፈጻሚነቱን ያቆመዋል እንጂ አያቋርጠውም ወይም አያፈርሰውም፡፡ በመሆኑም ከእገዳው በኋላም ቢሆን መድን ገቢው በመድን ሰጪው ጥያቄ ይሁን በራሱ አነሣሽነት አረቦኑን ቢከፍል ከከፈለበት ቀን አንስቶ ውሉ ተፈጻሚነቱን ሊቀጥል እንደሚችል በዚሁ የን.ሕ.ቁ. 666 ንዑስ ቁጥር /5/ ሥር ተጽፎ እናነባለን፡፡

መድን ሰጪው የተወዘፈው አረቦን እንዲከፈለው ከጠየቀበት ቀን አንስቶ የአንድ ወር ጊዜ ሲያልፍ ማለትም የእገዳው ተፈጻሚነት ከጀመረ በኋላ በን.ሕ.ቁ. 666 /4/ ሥር ሁለት አማራጮች ተሰጥተውታል፡፡ 1ኛ/ከላይ እንደተባለው በድጋሚ የተወዘፈው አረቦን እንዲከፈለው ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡[41] 2ኛ/ አንደኛውን አማራጭ ካልፈለገ ደግሞ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ ይችላል፡፡[42]

---

[41] ይህ መቼም ተግባራዊ መሆኑ አጠራጣሪ ይመስላል፣ ነገር ግን መድን ሰጪው የረዥም ጊዜ ደምበኝነትንና ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በድጋሚ ጥያቄ ለማቅረብ ይፈልግ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የን.ሕ.ቁ.. 666/4/ የእንግሊዝኛ ቅጂ "claim" ስለሚል በፍርድ ቤት ወይም በግልግል ዳኝነት መድረክ ላይ እንዲከፈለው ክስ ያቀርባል ማለት ነው ሊባል ይችላል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ከሕይወት መድን አንፃር መድን ሰጪው አረቦን ስላልተከፈለው ክስ ማቅረብ እንደማይችል ተጽፎ ስለምናይ የን.ሕ.ቁ.. 666/4/ ን ክስ ወደማቅረብ ልናጠቃልልው የምንችል ይመስላል፡፡

[42] ይህ ሁሉ ሆኖ ሕጉ መድን ሰጪው ውሉን እራሱ እንዲያፈርስ ወይም ፈርሷል ብሎ እንዲል መብት የከለከለው ይመስላል፡፡ ተዋዋዮች በልዩነት ካልተስማሙ ወይም ሕግ ካልፈቀደ ውል እንዲፈርስ መጠየቅ በፍርድ ቤት በኩል እንደሚሆን በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1784 ተመልክቷል፡፡

መድን ሰጪው በመጀመሪያው አማራጭ በመጠቀም የተወዘፈው አረቦን እንዲከፈለው ጠይቆ ከተከፈለው ውሉ እገዳው ተነስቶለት ውጤት መስጠት እንደሚጀምር ከን.ሕ.ቁ. 666 /5/ አባባል ስንገነዘብ፣ በሁለተኛው አማራጭ ሊጠቀም የፈለገ መድን ሰጪ ግን ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት[43] አማካኝነት ውሉን ሲያስፈርስ የውሉ መፍረስ የሚያስከትለውን ውጤት የንግድ ሕጉ አይናገርም፡፡ ምናልባት ያው በፍ.ብ.ሕ.ቁ 1815 መሠረት በተቻለ መጠን ተዋዋይ ወገኖች ከውሉ በፊት ወደነበሩበት ቦታ ይመለሳሉ ለማለት ይቻል ይሆናል፣ ሆኖም በን.ሕ.ቁ. 666/4/ መሠረት አንድ የመድን ውል ሲፈርስ ሁለቱንም ተዋዋይ ወገኖች በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1815 መሠረት ከውሉ በፊት ወደ ነበሩበት መመለስ አይቻልም፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው መድን ሰጪው ለውሉ ግዴታ ተጠያቂ የሚሆነው የተፈራው አደጋ ሲደርስ ወይም ጊዜ ሲሟላ ወዘተ ስለሚሆን ከርሱ ወደ መድን ገቢው የሚሄድ ነገር የለም፡፡ የን.ሕ.ቁ. 666 ተፈጻሚነት ራሱ የሚነሣው መድን ገቢው በገባበት ግዴታ መሠረት አረቦን ለመክፈል ሲዘገይ ስለሆነ መድን ገቢው ከሰጪው በተመላሽነት የሚጠይቀው ነገር አይኖርም፡፡

ይልቅ አከራካሪ ሊሆን የሚችለው አረቦኑ መከፈል ይገባው ከነበረበት ጊዜ አንስቶ ውለታው በሕግ ማለትም በን.ሕ.ቁ. 666/3/ መሠረት እስከታገደበት ጊዜ ድረስ መድን ሰጪው ላደጋው ኃላፊነት ስለነበረበትና He was on risk ለዚያ ጊዜ ደግሞ ሽፋን እንደሰጠ ስለሚቆጠር ለዚያ ጊዜ አረቦኑ ተሠልቶ መድን ገቢው እንዲከፍል ሊገደድ የሚችል ይመስላል፡፡ ይህን ገንዘብ መድን ሰጪው ባልተከፈለ አረቦንነቱ እንኳን ባያገኘው በኪሣራ መልክ ሊሰጠው የሚገባ ይመስላል፡፡ በነገራችን ላይ በን.ሕ.ቁ. 666 ሥር በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ቅጂዎች በተጻፉት ድንጋጌዎች መካከል ልዩነት አለ፡፡ በተለይም በእንግሊዝኛዉ ቅጂ በን.ቁ. (2) እና (4) ላይ “terminate” እና “termination” በአማርኛዉ ቅጂ ደግሞ “ለማፍረስ” እና “እንዲፈርስ” በተሰኙት ቃላት መካከል ሰፊ ልዩነት አለ፡፡ በእንግሊዝኛዉ ቅጂ ላይ የተጻፉቱ ቃላት በአማርኛ በትክክል ቢተረጎሙ ኖሮ “ማቋረጥ“ “መቋረጥ“ የሚል ትርጉም ሲኖራቸዉ በአማርኛዉ ቅጂ ላይ የተጻፉቱ ግን “ማፍረስ“ “መፍረስ“ የሚሉ ናቸዉ፡፡ በሌላ በኩል በ “መፍረስ“ እና በ “መቋረጥ“ መካከል ትልቅ የዉጤት ልዩነት አለ፡፡ በዉል ህግ ቋንቋ “መቋረጥ“ ወይም “ማቋረጥ“ የወደፊት ዉጤት ብቻ ሲኖረዉ ማለትም ዉሉ እስከተቋረጠበት ጊዜ ድረስ የተፈፀሙትን ግዴታዎች የማይነካ የተዋዋዮቹን የወደፊት ግዴታዎችን ብቻ የሚመለከት ሲሆን የዉል “መፍረስ“ ግን ወደ ኋላ ሄዶ ዉሉን ከምስረታዉ ጀምሮ የሚነካዉ፣ በዉሉ መሠረት የተፈፀሙትን ግዴታዎች እንዳልተፈፀሙ በማስቆጠር ወደ ኋላ የሚመልሳቸዉ እንደዚሁም ደግሞ ከዉሉ መፍረስ የተነሳ ወደፊት ሊፈፀሙ ይችሉ የነበሩትን ግዴታዎችንም ጭምር የሚመለከት ነዉ፡፡ በ “መቋረጥ“ እና በ “መፍረስ“ መካከል ባሉት እነዚህ ልዩነቶች መነጽር በን.ሕ.ቁ. 666 የተቀመጠዉን

---

[43] የን.ሕ.ቁ. 666/4/ “ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየቅ ይችላል” ስለሚል መድን ሰጪው የግድ በፍ/ቤት በኩል መሄድ ይኖርበታል ማለት ሲቻል በሌላ በኩል ግን ውሉን ከተዋዋይ ወገኖች አንዱ ሲያፈርስ /ፍርድ ቤት ሳይሄድ/ እንደሚቻል በፍ.ብ.ሕ.ቁ.1774 1786 እና 1787 ተመልክቶአልና ከነኝህ ቁጥሮች ባንደኛው መጠቀም ከቻለ መድን ሰጪው በገዛ ራሱ ውሉ ፈርሷል ሊል እንደሚችል ይገመታል፡፡

ስንመለከት መድን ሰጪው አረቦን እንዲከፈለው ጠይቆ በአንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ካልተከፈለዉ ዉሉን የማቋረጥ መብት ነዉ ያለዉ ወይንስ የማፍረስ? የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ የማይቀር ነዉ። አስገዳጅ በሆነዉ የአማርኛዉ ቅጂ መሠረት ከተሄደ መድን ሰጪው ዉሉን ከነዉጤቱ ማስፈረስ ሲችል በእንግሊዝኛዉ ቅጂ መሠረት ከተሄደ ደግሞ መድን ሰጪው ዉሉን በራሱ ሥልጣን በማቋረጥ በወደፊት ግዴታዎች ላይ ብቻ ዉጤት እንዲኖረዉ ማድረግ ይችላል።

ስለአረቦን ክፍያ የተጻፈው የን.ሕ.ቁ. 666 በሕይወት መድን ላይ ተፈጻሚ ያለመሆኑ በዚሁ ቁጥር በንዑስ ቁጥር /6/ ሥር ተደንግጓል። ስለሕይወት መድን የተደነገጉትን የንግድ ሕግ ቁጥሮች ስንቃኝ ስላልተከፈለ የኢንሹራንስ መግቢያ ገንዘብ በሚል ርዕስ ቁጥር 709 ስለዚሁ ጉዳይ የሚደነግግ መሆኑን እንረዳለን።

በን.ሕ.ቁ. 666 እና 709 መካከል ጉልቶ የሚታየው ልዩነት በቁጥር 666 ላይ የተጻፈው እንደተጠበቀ ሆኖ ውል የማፍረስና የተወዘፈው አረቦን እንዲከፈል ጥያቄ ወይም ክስ የማቅረቡ መብት ሰፋ ተደርጕ ለመድን ሰጪው ሲሰጥ በቁጥር 709 ላይ ግን 1ኛ/ ውዝፍ አረቦን እንዲከፈል ክስ ማቅረብ የተከለከለ መሆኑን፣ እና 2ኛ/ የአረቦኑ መወዘፍ በቁጥር 709/2/ ሥር በተመለከተው ሁኔታ ካልተሸፈነ ውሉን ማፍረስ እንደማይቻል እንገነዘባለን።

በን.ሕ.ቁ. 709/2/ ሥር እንደተመለከተው አንድ መጽናት ከጀመረ ገና ሶስት ዓመት ያልሞላው የሕይወት መድን ውል ተገብቶ በውሉ መሠረት በየዓመቱ መጀመሪያ ላይ መከፈል የሚገባው አረቦን ኖሮ ለምሳሌ በ3ኛው ዓመት መግቢያ ላይ መከፈል የነበረበት ሳይከፈል ቢቀር መድን ሰጪው እንዲከፈል ጥያቄ ያቀርብና ጥያቄ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለው ውሉን ሊያፈርስ እንደሚችል እናያለን።[44]

ይሁን እንጂ ፖሊሲው ውሉ መጽናት ከጀመረ አንስቶ እጅግ ቢያንስ ሶስት ዓመታዊ የአረቦን ክፍያዎች የተከፈሉበት ከሆነና ለምሣሌ የአራተኛው ዓመት አረቦን በወቅቱ ካልተከፈለው መድን ሰጪው እንዲከፈለው ጥያቄ ማቅረብ እንደሚችልና ጥያቄ ባቀረበ በ1ወር ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለው ውሉ ውድቅ መሆኑ ወይም መፍረሱ ቀርቶ መድን ሰጪው ከዚህ በታች ከተመለከቱት ሁለት አማራጮች አንዱን መፈጸም እንዳለበት በን.ሕ.ቁ. 709/3/ ሥር ተደንግጕአል።

አማራጮቹም:-

1/ ለተከፈለው ገንዘብ ተመጣጣኝ ፖሊሲ መስጠት ወይም

2/ የተስማሙበትን ዋና ገንዘብ ወይም በሕይወት እስካለ ድረስ የሚከፈለውን ገንዘብ በን.ሕ.ቁ. 656 መሠረት በሚወጣው ደንብ መሠረት መቀነስ ናቸዉ።

---

[44] በን.ሕ.ቁ. 666/3/ ሥር የተመለከተው የእገዳ ጊዜ በቁጥር 709 ላይ አይታይም።

የመጀመሪያውን አማራጭ ለመከተል የፈለገ መድን ሰጪ አሁን ሥራ ላይ ባለውና የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከሚጠቀምበት የሕይወት መድን ፖሊሲ ላይ "የአረቦን ክፍያ ሲቋረጥ" በሚለው ክፍል ሥር እንደተመለከተው የሚያደርገው "የአረቦን ክፍያው በተቋረጠበት ጊዜ ውሉ ባፈራው የጥሬ ገንዘብ ዋጋና መድን በገባው ሰው ዕድሜ ላይ የተመሠረተ የተቀነሰና በሙሉ የተከፈለበት የመድን ፖሊሲ መስጠት" ሲሆን ሁለተኛውን አማራጭ ለመከተል ከፈለገ ግን አሁንም በዚሁ በሕይወት መድን ፖሊሲ ላይ እንደተመለከተው ማናቸውንም በመድን ገቢው ላይ የሚፈለገውን ዕዳ ቀንሶ ውሉ ያፈራውን የጥሬ ገንዘብ ዋጋ በጥሬ ገንዘብ ባንዴ ይከፍላል ወይም ደግሞ በተደረገው ቅናሽ መሠረት መድን ገቢው በሕይወት እስካለ ድረስ በየጊዜው የሚከፈለውን ገንዘብ ይሰጠዋል፡፡

ከዚህ በላይ በን.ሕ.ቁ. 709/3/ ከተጠቀሱት ሁለት አማራጮች በተጨማሪ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምበት 3ኛ አማራጭ በሕይወት መድን ፖሊሲ ላይ ይታያል፡፡ ይኸውም "የተራዘመ ተርም መድን" /ኤክስተንድድ ተርም ኢንሹራንስ/ በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ሲሆን ተግባራዊነቱም "ውሉ የሚኖረውን የተጣራ የጥሬ ገንዘብ ዋጋንና የመድን ገቢውን ዕድሜ እግምት ውስጥ በማስገባት ከመድን ገቢው ላይ የሚፈለገውን ማንኛውንም ዕዳ ቀንሶ መድን ገቢው በደረሰበት ዕድሜ የፖሊሲው የጥሬ ገንዘብ ዋጋ የሚገዛውን በማስላት ውሉ ለዚያን ያህል እንዲቀጥል ማድረግ ሲሆን" በእንግሊዝኛው የሕይወት መድን ፖሊሲ ቅጹ ላይ እንደተመለከተው የፖሊሲው የጥሬ ገንዘብ ዋጋ የመድን ገቢውን ዕድሜ ተንተርሶ የተራዘመ ተርም መድን ገዝቶ የሚተርፍ ከሆነ መድን ገቢው የተራዘመው ጊዜ ሲያልቅ በሕይወት ኖሮ ከተገኘ ተራፊው ገንዘብ እንደ አንድ ጊዜ አረቦን ተቆጥሮ ተጨማሪ ገንዘብ እንደሚያስገኝለት ተመልክቷል፡፡

## ከተዋዋይ ወገኖች ያንደኛው መክሠር

የን.ሕ.ቁ 671-673 ድንጋጌዎች በተመለከተ ድንጋጌዎች ሲረቀቁ ምን ታሳቢ እንደተደረገ ፒተር ዊንሺፕ እንደሚከተለዉ ይገልጹታል፦

> The effects of bankruptcy, of death and of the assignment of the object insured are regulated so as to maintain the effects of the insurance as far as possible, while at the same time safeguarding the parties' freedom to terminate the contract.[45]

*የተዋዋይ ወገኖችን ዉሉን የማቋረጥ ነፃነት ሳይነካ ከሥረት፣ሞትና መድን የተገባለት ንብረት መተላለፍ የሚያስከትሏቸዉን ዉጤቶች ለመቆጣጠር እንዲቻል በተቻለ መጠን ዉሎቹ ዉጤታማ ሆነዉ እንዲቀጥሉ ተደርጓል፡፡* (ትርጉም የፀሃፊዉ)

[45] Peter Winship, ቀደም ሲል በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 15 የተመለከተዉ ገጽ 83

ይህንኑ መሠረት አድርገን ድንጋጌዎቹን ከዚህ በታች እንመለከታቸዋለን።

በን.ሕ.ቁ. 671/1 ሥር ሠፍሮ እንደምናገኘው አንድ መድን ገቢ ከከሠረ የመድን ውሉ በዚሁ ምክንያት ብቻ አይፈርስም። የከሣሪው መድን ገቢ ንብረት ጠባቂ ባለአደራዎች በውሉ ተጠቃሚና ለመድን ሰጭው ለሚከፈለው አረቦን ተጠያቂ ባለዕዳ ሆነው የመድን ውሉ ፀንቶ ይቆያል።

በን.ሕ.ቁ. 671/1/ ሥር የሚታየው ድንጋጌ ሁሉንም መድን ገቢ የሚመለከት ጉዳይ አይደለም። የሚመለከተው የከሠረን መድን ገቢ ሲሆን ማንኛውም መድን ገቢ ደግሞ ከሠረ ሊባል እንደማይቻል መገንዘብ ያስፈልጋል። በዚህ በያዝነው ንዑስ ርዕስ ምን ዓይነት መድን ገቢ "ከሠረ" ሊባል እንደሚቻልና "ክሥረት" ራሱ ምን እንደሆነ "ንብረት ጠባቂ ባለአደራዎች" ማለት እነማን እንደሆኑ በመጠኑም ቢሆን ለአንባብያን ማስተዋወቁ አስፈላጊ ይሆናል።

በመጀመሪያ "ከሠረ" የሚለው አባባል ተፈጻሚነቱ የሙያ ሥራው አድርጐ ጥቅም ለማግኘት ሲል በን.ሕ.ቁ. 5 ከተዘረዘሩት ሥራዎች መካከል አንዱን በሚሠራ በማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ላይና ከእሽሙር ማሕበር በስተቀር በመመሥረቻ ጹሑፍ መሠረት ወይም በተግባር በን.ሕ.ቁ. 5 ከተዘረዘሩት ሥራዎች አንዱን በሚሠራ የንግድ ማሕበር ላይ ብቻ መሆኑን መረዳቱ ጠቃሚ ነው።[32] በሌላም በኩል የንግድ ማሕበራትን በተመለከተ በን.ሕ.ቁ.10(2) መሠረት በኢትዮጵያ ዉስጥ ዕዉቅና የተሰጣቸዉ ሁለት ኩባንያዎች ማለትም የአክሲዮን ማህበራትና ሐላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበራት የተቋቋሙት በን.ሕ.ቁ. 5 ከተዘረዘሩት ሥራዎች አንዱን ለመሥራት ይሁን አይሁን ዓይነተኛ የንግድ ጠባይ ያላቸዉ ማህበራት መሆናቸዉ መዘንጋት የለበትም።[46] "ከሠሩ" ልንላቸው የምንችለው እነማንን መሆኑን ካወቅን "ክሥረት" ራሱ ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ባጭሩ መልስ ለመስጠት ይሞከራል። አንድ ግለሰብ ነጋዴ ወይም የንግድ ማሕበር እንደከሠረ የሚቆጠረው ይኸው ግለሰብ ነጋዴ ወይም ዓይነተኛ የንግድ ጠባይ ያለው የንግድ ማሕበር ማንኛውንም ከንግዱ ሥራ ጋራ የተያያዘውን ዕዳውን መክፈል ያቋረጠና መክሠሩ በፍርድ የተወሰነ ሲሆን መሆኑን የንግድ ሕጉ ይገልጻል።[47]

ያንድ ግለሰብ ነጋዴ ወይም የንግድ ማሕበር መክሰር የሚታወቀው ነጋዴው ወይም የንግድ ማሕበሩ ከንግድ ሥራው ጋር የተያያዙትን ዕዳዎች ለመክፈል

---

[46] የንግድ ህጉ በአንድ በኩል የንግድ ማህበራትን ባብዛኛዉ በመመሥረቻ ጽሁፍ እንሠራለን ብለዉ በሚሉት ወይም በተግባር በሚሠሩት ላይ ተመሥርቶ ዓይነተኛ ንግድ ጠባይ ያላቸዉ እና የሌላቸዉ በማለት በዓላማቸዉ ላይ ተመሥርቶ በሁለት ጎራ ሲከፍላቸዉ፣ በሌላ በኩል ግን የንግድ ማህበራቱ የሚቋቋሙበት ፎርም ብቻዉን ከሁለቱ ባንደኛዉ ጎራ ዉስጥ እንዲደመሩ ያደርጋቸዋል፣ ከዚህ የተነሳ በህጉ ዕዉቅና የተሰጣቸዉ ሁለቱ ኩባንያዎች ዓላማቸዉ ምንም ይሁን ዓይነተኛ ንግድ ጠባይ ያላቸዉ ማህበራት ተብለዉ ተወስደዋል።

[47] የን.ሕ.ቁ. 5፣ ከቁጥር 10 እና ከቁጥር 968 ጋር ተዳምሮ ሲታይ

ያለመቻሉን ከሚገልጹ ከማንኛውም ድርጊቶች፣ፍሮነገሮች (facts) ወይም ሠነዶች[48] ቢሆንም ቅሉ ነጋዴው ወይም ማሕበሩ ማንኛውንም ዕዳ መክፈል በማቋረጡ ብቻ ከሠረ ሊያሰኘው እንደማይችልና አንድ ሰው ወይም ማሕበር ከሠረ ለማለት የግድ ከንግድ ሥራው ጋር የተያያዘውን ዕዳ መክፈል ማቋረጥና የፍርድ ቤት የክሥረት ውሣኔ መሠጠት እንዳለበት እንረዳለን::[49] ሆኖም የአንድ ግለሰብ ነጋዴ ወይም የንግድ ማሕበር ዕዳውን መክፈል ማቋረጥ ለፍ/ቤት ቀርቦ የክሥረት ውሳኔ ባይሰጥም በመክሠር ላይ በሚደረግ የማጭበርበር ወይም ሌሎች የወንጀል ሥራዎች የወንጀል ፍ/ቤት የቅጣት ፍርድ ሊፈረድ ይችላል::[50]

የክሥረትን ሁኔታ ለማስታወቅ የሚሰጠው ፍርድ የኪሣራውን ሥራ የሚመረምር አንድ ዳኛና አንድ ወይም ቁጥራቸው ቢበዛ ከሶስት የማይበልጥ የከሠረው ሰው ወይም የንግድ ማሕበር ንብረት የሚያስተዳድሩ ንብረት ጠባቂዎች መምረጥ /መሾም/ እንዳለበት የንግድ ሕጉ ሲደነግግ[51] ዋናው የንብረት ጠባቂዎች ሥራ የከሠረው ሰው ወይም ንግድ ማሕበርን ማስተዳደርና የአስተዳደር ሥራንም ሲያከናውኑ ግለሰቡ ወይም ማሕበሩ ከንግድ መዝገብ እስከሚፋቅ የገንዘብ ጠያቂዎችን መብት ለመጠበቅ የሚጥሩ ባለአደራዎች ናቸው::

ወደ ን.ሕ.ቁ. 671 መለስ ስንል የመድን ገቢው መክሠር ፖሊሲውን ወዲያውኑ (automatically) እንደማያቋርጠውና ምንም እንኳን መድን ገቢው ቢከሥርም በፍርድ ቤት የተሾሙት ንብረት ጠባቂ ባለአደራዎች በዚሁ የንግድ ሕግ ቁጥር መሠረት ማለትም በሕግ የመድን ውሉ ተጠቃሚ ሆነው ውሉ እንደሚቀጥል እንገነዘባለን:: የን.ሕ.ቁ 671/2/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቁጥር 671/1/ መድን ገቢው በመክሠሩ ምክንያት ብቻ ውሉ አይፈርስም ብሎ ሲያስቀምጥ በፍርድ ቤት የተሾሙት የከሣሪውን መድን ገቢ ንብረት ጠባቂ ባለአደራዎችን የመድን ውሉ ፀንቶ እስከቆየ ድረስ ለአረቦን ተጠያቂ ባለዕዳዎች አድርጓቸዋል:: እዚህ ላይ ግልጽ መደረግ ያለበት ነገር ንብረት ጠባቂ ባለአደራዎች በውሉ ተጠቃሚነታቸው ሆነ ለአረቦን ተጠያቂነታቸው በግላቸው እንዳልሆነ ነው:: ተጠቃሚነታቸው ዞሮ ዞሮ ለዚያው ለከሠረው ግለሰብ ወይም የንግድ ማሕበር ንብረት ጠባቂ ባለአደራዎች ከመሆናቸው አንፃር እንጂ በግላቸው የመድኑ ውል ፖሊሲ የሚያስገኘውን ገንዘብ እንዲያገኙ አለመሆኑን ነው:: ይህንን ስንል ምናልባት ከክሥረት ውሣኔ በኋላ የመድን ውሉ ፀንቶ እያለ መድን የተገባለት አደጋ ቢደርስና መድን ሰጪው ካሣ ቢከፍል ካሣውን ተቀብለው ከከሣሪው ግለሰብ ወይም የንግድ ማሕበር ንብረት ይደምሩለታል ማለት ሲሆን ለአረቦኑ ተጠያቂነታቸው ከዚያው ከከሠረው ሰው ወይም የንግድ ማሕበር ሀብት ነው እንጂ በግል ከኪሣቸው አይደለም:: ንብረት ጠባቂ በለአደራዎች በህግ የተሰጣቸዉ ስልጣን የከሠረዉን ሰዉ ንብረት

---

[48] የን.ሕ.ቁ. 971

[49] የን.ሕ.ቁ. 970

[50] የን.ሕ.ቁ. 970/2/ እና በ1997 ዓ.ም የወጣዉን የወንጀል ህግ ከአንቀጽ 725 እስከ 733 ያሉትን ይመልከቱ::

[51] የን.ሕ.ቁ. 981

በመርማሪዉ ዳኛ ጥበቃ ሥር ሆኖ ማስተዳደር እና ተራ ገንዘብ ጠያቂዎችን በሙሉ በሶስተኛ ወገኖች ፊት የመወከል ነዉ።[52]

በን.ሕ.ቁ. 671 ላይ መድን ገቢው በመክሠሩ ምክንያት ብቻ ውሉ አይፈርስም ቢልም የመድን ገቢው ክሥረት በፍ/ቤት ከተወሰነ ጀምሮ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ውሉን ወይ መድን ሰጪው ወይም ንብረት ጠባቂዎቹ ሊያፈርሱት እንደሚችሉ በን.ሕ.ቁ. 671/2/ ሥር ተደንግጐአል።

በአንድ በኩል በን.ሕ.ቁ. 671 "ተቃራኒ ውል ቢኖርም" የሚል አባባል ስለሌለ መድን ሰጪው በፖሊሲዎች ላይ "የመድን ገቢው ክስረት ውሉን ወዲያውኑ ከፍጻሜ ያደርስዋል" ብሎ ማስገባት የሚችል ቢመስልም በሌላ በኩል ግን ይህ ዓይነቱ ስምምነት ካጠቃላይ የን.ሕ.ቁ. 671/1/ ድንጋጌ መንፈስ ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ አይመስልም።[53]

ለማነፃፀር ያህል በባህር ሕግ በቁጥር 299 ሥር የተደነገገዉን መመልከቱ መልካም ነው። በእንግሊዝኛ የህጉ ቅጂ በንኡስ ቁጥር (1) "the underwriter may terminate policies in force in the event of the bankruptcy of the assured" ተብሎ ተደንግጐአል። ይህ ድንጋጌ መድን ገቢዉ የከሠረ እንደሆነ ዉሉን የማቋረጥ መብትን ለመድን ሰጪዉ ሲሰጥ የንዑስ ቁጥሩ የአማርኛ ቅጂ ግን ዉሉን የማፍረስ መብት ነዉ የሚሰጠዉ።[54] ሎቹን የባህር ሕጉን የቁጥር 299 ድንጋጌዎች አንባቢዉ እንዲያዉቃቸዉ በግርጌ ማስታወሻነት ተዘርዝረዋል።[55]

---

[52] የን.ሕ.ቁ. 985(1)

[53] ሕጉ በተለያዩ ሁኖቴዎች የመድን ውል ፖሊሲ ወደ ሌላ ተላልፎ እንዲቀጥል የሚያዝበት ዋነኛው ምክንያት የ"risk" ጥያቄ በውስጡ ስላለ ሰዎችን ድንገት ለአደጋ እንዳይጋለጡ መሸጋገሪያ ጊዜ ለመስጠት ሳይሆን አይቀርም።

[54] የባህር ሕግ ቁጥር 299(1) የአማርኛዉ ቅጂ የሚለዉ" ኢንሹራንስ የገባዉ ሰዉ የከሠረ እንደሆነ ኢንሹራንስ አድራጊዉ የተጀመረዉን ኢንሹራንስ ሁሉ ማፍረስ ይችላል" ነዉ።

[55] ቁጥር 299(2) ለኢንሹራንሱ የሚከፈለዉ ገንዘብ በጊዜዉ ያልተከፈለና ኢንሹራንስ የተደረገለት ሰዉ በሃያ አራት ሰዓት ዉስጥ እንዲከፍለዉ ማስጠንቀቂያ ከላከለት በኋላ ይህ የማፍረስ ችሎታ ይኖረዋል።

(3) የዉሉ መፍረስና ግዴታዎች እንዲፈፀሙ የሚደረገዉ ማስጠንቀቂያ በሬኮማንዴ ደብዳቤ ወይም በቴሌግራም ሊደረጉ ይችላሉ።

(4) የሚከፈሉት የጉዳት ኪሳራዎች ሳይነኩ የዉሉ መፍረስ ይደርሳሉ ተብለዉ ለሚያስጉት አደጋዎች (ሪስክ) ከተወሰኑት ጊዜዎች ባልደረሱት ጊዜዎች መጠን ለኢንሹራንስ ከተለፈለዉ ገንዘብ ላይ ተመላሽ ይደረጋል።

(5) ኢንሹራንስ የገባዉ ሰዉ ያልከፈለዉን የኢንሹራንስ ዋጋ ሦስተኛ ወገን ከከፈለ ማንኛዉም አደጋ ከመድረሱና የዉሉ መፍረስ ማስታወቂያ ከመላኩ በፊት ኢንሹራንስ በተላለፈለት በቅን ልቡና ተጠቃሚ በሆነ ሦስተኛ ወገን ላይ የዉሉ መፍረስ ዉጤት አይኖረዉም።

(6) ኢንሹራንስ አድራጊዉ በከሠረ ጊዜ ኢንሹራንስ የገባዉ ሰዉ እንደዚሁ ያሉ መብቶች ይኖሩታል።

የመድን ሰጪው መክሰር የግድ ውሉን ወደ ፍጻሜ እንደሚያመጣው በን.ሕ.ቁ. 671/3/ ላይ ተመልክቷል። የመድን ገቢው ክሥረት የግድ የውሉን መቀጠል ባያቆመውም የሰጪው ክስረት ግን የክስረቱ ውሣኔ በተሰጠ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሉን እንዲያቋርጠው ሕግ ደንግጉአል። የመድን ሰጪው ክስረትና በዚህም ምክንያት የውሉ /ማለቅ/ ማቋረጥ ምን ውጤት እንደሚያስከትል ሕጉ ያለዉ ነገር ባይኖርም እስከ ክሥረቱ ውሣኔ ድረስ የመድን ፖሊሲዎቻቸው የበሰሉ መድን ገቢዎች የከሣሪው መድን ሰጪ ገንዘብ ጠያቂ /ክሬዲተርስ/ ሲሆኑ እንደሚችሉ ሲገመት ፖሊሲዎቻቸው ያልበሰሉ መድን ገቢዎች ከውሉ መቋረጥ ባሻገር ላለው ጊዜ የከፈሉትን አረቦን ከከሣሪው መድን ሰጪ መጠየቅ መገመት ይቻላል።

የን.ሕ.ቁ. 671 ድንጋጌ በካሣ መድኖች ላይ ብቻ ተፈጻሚ ስለመሆኑ ለመረዳት በንግድ ሕጉ ውስጥ የሠፈሩትን የካሳ ያልሆኑ መድኖችን የሚመለከቱትን ድንጋጌዎች ማየቱ በቂ ነው ። ይህ ንዑስ ርዕስ ከማጠቃለሉ በፊት ሌላው መነሣት ያለበት ነጥብ የን.ሕ.ቁ. 671 እና ምናልባትም ተከታዮቹ የመድን ውል አስተላላፊ ድንጋጌዎች ናቸው ወይንስ የመድን ጥቅም? የሚለውን ጥያቄ የን.ሕ.ቁ. 673 ን ስንመለከት የምንመለስበት መሆኑን ነዉ።

## የመድን ውል ተጠቃሚ መሞት

ስለመድን ፖሊሲ በሕግ መተላለፍ የሚያወሳው ሌላው ቁጥር የን.ሕ.ቁ. 672 ሲሆን በዚህ ቁጥር ንዑስ ቁጥር /1/ ላይ እንደተመለከተው አንድ የንብረት መድን ወይም የሃላፊነት መድን ሽፋን[56] የገዛ ሰው ቢሞት የመድኑ ውል መብት ወደ ወራሾቹ ተላልፎ እንደሚቀጥል እናነባለን። ይህ የቁጥር 672/1/ ድንጋጌ ተፈጻሚነቱ ተዋዋይ ወገኖች በሚያደርጉት ተቃራኒ ስምምነት እንደማይገታ ተቃራኒ የውል ቃል ቢኖርም እንኳ በሚለው የራሱ የሕጉ ሐረግ ስለተነገረ ማንኛውም በፖሊሲው ውስጥ ይህን የ 672/1/ን አባባል የሚቃረን ስምምነት ካለ ውድቅ ይሆናል። የመድን ገቢው መሞት ውሉን ወዲያውኑ (forthwith) አያቋርጠው እንጂ መድን ገቢው በሞተ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ወራሾቹ ወይም መድን ሰጪው ውሉን ማቋረጥ እንደሚችሉ በንዑስ ቁጥር /2/ ሥር ተጽፎአል። ከፈለጉም ውሉን ከመቀጠል የሚያግዳቸው ምንም ነገር የለም።

---

[56] ለሞት ከተደረገ የሕይወት መድን አንፃር አንድ መድን ገቢ ቢሞት ፖሊሲው ገንዘብ ሊጠየቅበት የሚችል የበሰለ ፖሊሲ ይሆናል። ተጠቃሚውም ፖሊሲው የሚያስገኘው ገንዘብ እንዲከፈለው ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። ከውሉ ምሥረታ ቀን ጀምሮ ወደፊት ለዚህን ያህል ዓመት ወይም እስከ ተወሰነ ቀን /ዓመተ ምሕረት/ ወዘተ በሕይወት ኖሬ ከተገኘሁ የተወሰነ ገንዘብ ትከፍለኛለህ በሚል የተገዛ ፖሊሲ ከሆነ በውሉ መሠረት ገንዘብ ሊገኝ የሚችለው መድን ገቢው በውሉ ውስጥ በተመለከተው ቀን በሕይወት ኖሮ ሲገኝ ብቻ ነው። /የን.ሕ.ቁ. 702/

## መድን የተገባለትን ንብረት ስለማስተላለፍ

ከመድን ሰጪው ፈቃድ ውጪ በሆነ ሁኔታ ተቃራኒ ስምምነት ቢኖርም ባይኖርም በን.ሕ.ቁ. 673 /1/ ላይ በግለጽ ተጽፎ እንደሚገኘው መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ በሽያጭ ወይም በስጦታ[57] ሲተላለፍ የመድኑ ውልና መብት በሙሉ ንብረቱ ወደ ተላለፈለት ሰው ይተላለፋል። ሕጉ እንደዚህ ቁልጭ ባለ ሁኔታ ቢቀመጥም የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች አንዳንዶቹን[58] ስናይ መድን የተገባለት ንብረት በሽያጭ ወደ ሌላ ሲተላለፍ የመድን ውሉ ወዲያውኑ እንደሚቋረጥ ተመልክቷል።

ምናልባት በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 58 ላይ ለምሣሌነት በተጠቀሱት ሁለት ፖሊሲዎች ውስጥ መድን ሰጪው ንብረቱ በሽያጭ ሲተላለፍ ከተሸጠበት ጊዜ ጀምሮ ፖሊሲው ይቋረጣል ብሎ ያሠፈረው በን.ሕ.ቁ. 673/2/ ሥር ሕግ ውሉን በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ለማቋረጥ ለርሱም ሆነ ንብረቱ ለተላላፈለት ሰው መብት ስለሚሰጥ ይሆናል ብሎ መጠራጠር ይቻል ይሆናል፣ ነገር ግን ይህ በንዑስ ቁጥር /2/ ለመድን ሰጪውና ንብረቱ ለተላለፈለት ሰው የተሰጠው መብት በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር የተደነገገዉን በሚቃረን ሁኔታ ተቋዋዮቹን ማገልገል የለበትም።

የን.ሕ.ቁ 673/1/ ተፈጻሚነት መድን ሰጪው በሚጠቀምባቸው እንደ የግል ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን ፖሊሲና የንግድ ተሽከርካሪ ፖሊሲዎች ላይ ተጽፎ የሚታየውን ዓይነት የውል ቃል ከግምት ውስጥ ሳያስገባ መሆኑ "ተቃራኒ የውል ቃል ቢኖርም" በሚል ሐረግ ተመልክቷል። ከዚህ በላይ በን.ሐ.ቁ. 671 እና 672 ላይ የሠፈሩትን በተመለከተ በተብራራዉ መሠረት የቁጥር 673/1/ እና /2/ ጥምር መልዕክትም መድን የተገባለት ንብረት ከተላለፈ በኋላ ውሉ የግድ ንብረት በተላለፈለት ሰውና በመድን ሰጪው መካከል መቀጠል አለበት ሳይሆን ሕግ ሊከላከል የፈለገው መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ በመተላለፉ የውሉን በዚሁ ምክንያት ብቻ ወዲያውኑ መቋረጥ ነው። ለምሳሌነት በተጠቀሱት ሁለት ፖሊስዎች ላይ የሠፈረው ግን በቀጥታ በን.ሕ.ቁ. 673/1/ ሥር የተጻፈውን የሚቃረን ይመስላል። ሲሆን ንብረት ካስተላለፈው መድን ገቢና በመድን ሰጪው መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት ፖሊስው ለሶስት ወርና ከዚያ በላይ የሚቆይ ከሆነ ውለታው በአዲሱ ንብረት በተላለፈለት ሰውና በመድን ሰጪው መካከል እስከ ሶስት ወር ፀንቶ መቆየት እንዳለበት ሲገመትና ንብረት የተላለፈለትም ሰው ይህንን መከራከሪያ ሊያደርግ እንደሚችል ቢታይም መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ ከተላለፈ ጊዜ ጀምሮ 3 ወር ሳይሞላ ውሉን ከሁለት አንዳቸው ማቋረጥ እንደሚችሉ ግን አያከራክርም።

---

[57] በመያዣነት ወይም በአላባ ስምምነት ይዞታ ሲተላለፍ ጉዳዩ በን.ሕ.ቁ.673 ሥር ይሸፈን አይሸፈን ሊያከራክር ቢችልም ለጊዜው በግዢ ወይም በስጦታ ብቻ ስለሚተላለፍ ንብረት ማውሳቱ ብቻ በቂ ይሆናል።

[58] ለምሳሌ የግል ተሽከርካሪ የ3ኛ ወገን ፖሊሲና የንግድ ተሽከርካሪ ፖሊሲን ይመልከቱ።



Law Library
A. A. University
Addis Ababa

ምናልባት በን.ሕ.ቁ. 666፣ 668፣ 669፣ እና 671፣ ላይ የተመለከተው የአንድ ወር ጊዜ በተለይም ደግሞ በን.ሕ.ቁ. 666/3/ እና በቁ. 668/2/ /ሀ/ ሥር ሠፍሮ የሚገኘው መድን ሰጪው ውሉን ለማፍረስ አጅግ ቢያንስ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ መስጠት እንደሚያስፈልገው የሚናገሩት ድንጋጌዎች መድን ሰጪው መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ መተላለፉን ካወቀ ጊዜ ጀምሮ ውሉን ለማፍረስ ከፈለገ ቢያንስ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ንብረት ለተላለፈለት ሰው መስጠት እንዳለበት ይጠቁማሉ ለማለት ይቻላል:: መድን ሰጪው ውሉን በሰስት ወር ጊዜ የማፍረስ መብቱን ባግባቡ ሊጠቀምበት ከፈለገ ማድረግ የሚችለው ወይም የሚገባው መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ መተላለፉን እንዲያስታውቅ ወይም በንብረት አስተላላፊው ላይ ወይም ሕግ የውሉ መብት ተጠቃሚ ባደረገው ንብረት በተላለፈለት ሰው ላይ የማስታወቅ ግዴታን መጣል እንጂ የሕጉን መንፈስ በሚቃረን ከዚህ በላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 58 ላይ በተጠቀሱት ሁለት ፖሊሲዎች ላይ ተጽፎ እንደምናነበው ማድረግ የለበትም::

በርግጥ የመድን ሽፋን ያለው ንብረት ለሌላ ሲተላለፍ መድን ሰጪው ውሉ ወዲያውኑ እንዲቋረጥ አድርጐ እንዲያዘጋጅ የሚገፋፉት በርካታ አሳማኝ ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉምና ከነኚህ ውስጥ ዋነኛው የንብረት መተላለፍ መድን የተገባለትን አደጋ ሊያከብድ የመቻሉ ጉዳይ ቢሆንም መድን ሰጪው ሕግ ንብረቱ ለተላለፈለት ሰው የሚሰጠውን መብት ከሕጉ መንፈስ ውጪ ሊያጠብበት አይገባም፣ አይችልምም::

በጀርመን ፌዴራል ሪፑብሊክ እ.ኤ.አቆጣጠር ከ1910 ጀምሮ[59] መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ ሲተላለፍ የመድኑ ውል መብትና ግዴታ በሙሉ ከአስተላላፊው መድን ገቢ ንብረቱ ወደ ተላለፈለት ሰው እንደሚሸጋገር ተደንግጐ ይገኛል::[60] ይህም ስለውሉ መተላለፍ ምንም ዓይነት ውለታ ማድረግ ሳያስፈልግ እንደሆነና የግድ መደረግ ያለበት ነገር ቢኖር መድን የተገባለት ንብረት ለሌላ መተላለፉን ለመድን ሰጪው ማስታወቅ መሆኑን ስንረዳ[61] አለማስታወቅም መድን ሰጪውን ከኃላፊነት ነፃ የሚያደርገው ማስታወቅ ከሚገባበት ቀን ጀምሮ መድን የተገባለት አደጋ የደሰው የአንድ ወር ጊዜ ካለፈ በኋላ ከሆነ ነው ተብሎ በዚሁ እ.ኤ.አ. ከ1910 ጀምሮ ሥራ ላይ በዋለው በጀርመን የግል መድን ሕግ በ71ኛው ሴክሽን ላይ ተጽፎ እናነባለን::[62] ከዚሁ በመነሳት ሚስተር ፖተርሰን በጀርመን የግል መድን ሕግ መድን የተገባለት ንብረት ሲተላለፍ የመድኑ ውሉ መብት ንብረቱ ለተላለፈለት ሰው መሸጋገር ምንም እንደሚያከራክርና ይኸውም መብት ወዲያውኑ

---

[59] Edwin W. Patterson "The Transfer of Insured Property in German and American Law," Columbia Law Review, Vol. 29 (1929) pp.691 ff.

[60] በግርጌ ማስታወሻ ቁ.59 የተመለከተዉ ገጽ 693::

[61] በግርጌ ማስታወሻ ቁ.59 የተመለከተዉ::.

[62] በግርጌ ማስታወሻ ቁ.59 የተመለከተዉ::.

ንብረቱ ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለአንድ ወር መድን ሰጪውን ለመድኑ ዋስትና ንብረቱ ለተላለፈለት ሰው ተገዳጅ እንደሚያደርገው ይናገራሉ።[63]

በአሜሪካና በእንግሊዝ አገር ባጠቃላይ አነጋገር ምናልባት በንብረቱ ማስተላለፊያ ውል ላይ ወይም በሌላ ተጨማሪ ውል የመድን ውልም ከንብረቱ ጋር አብሮ ተላልፎአል ካልተባለ በስተቀር የንብረቱ መተላለፍ ብቻውን የፖሊሲውን መተላለፍ እንደማያስከትል ይነገራል።[64]

በእንግሊዝ አገር መድንና ተያይዘው ያሉትን ጥቅማጥቅሞችን የማስተላለፉ ጉዳይ ከሶስት አቅጣጫ ነው የሚታየው። እነኚህም 1ኛ/ የተገባለትን ንበረት ከማስተላለፍ አኳያ 2ኛ/ አንድ የመድን ውል የሚያስገኘውን ጥቅም ከማስተላለፉ አኳያ እና 3ኛ/ የመድን ውል ከማስተላለፍ አኳያ ሲሆን በኢትዮጵያ ሕግ ግን የሕይወት መድን ልዩ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የንብረት መድንን በሚመለከት እነኚህ የተጠቀሱት ሶስት ሁኔታዎች ተለይተው የሚታዩ አይመስሉም። በን.ሕ.ቁ. 671፣ 672 እና 673 ላይ እንደተመለከተው ሁሉም የውሉን መተላለፍ የሚያስከትሉ ይመስላል።

**በውሉ የተመለከተው አደጋ በደረሰ ጊዜ**

**ሀ. የመድን ገቢው ኃላፊነት**

በን.ሕ.ቁ. 670/1/ ላይ እንደተደነገገው አንድ መድን ገቢ ከአቅሙ በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ማሳወቅ ያልቻለ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር መድን ሰጪው ሽፋን የሰጠበት አደጋ መድረሱን እንዳወቀ ወዲያውኑ ወይም አጅግ ቢዘገይ በአምስት ቀናት ውስጥ ለመድን ሰጪው ማስታወቅ አለበት።

ከዚህ በላይ በውሉ ምሥረታ ጊዜ እንደዚሁም ደግሞ ውሉ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ተፈራው አደጋ መድረስ ባለው ጊዜ የተዋዋይ ወገኖችን መብትና ግዴታ ለመመልከት ተሞክሮአል። በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር የምናየው ተፈርቶ መድን የተገባለት አደጋ ሲደርስ መድን ገቢው ምን ማድረግ እንዳለበት ሲሆን ቀጥሎ በመግቢያው ላይ እንደተመለከተው በን.ሕ.ቁ. 670/1/ ሥር የተጣለበትን ግዴታ እንመረምራለን።

በን.ሕ.ቁ 670/1/ የአማርኛው ቅጂ መሠረት መድን ገቢው ማስታወቅ የሚገደደው መድን ሰጪው ኃላፊነት የወሰደበትን አደጋ መድረስ እንጂ ሌላ አደጋ መድረሱን አይደለም። ለምሣሌ በን.ሕ.ቁ. 677 ሥር ተጽፎ እነደምናነበው መድን የተገባለት ንብረት ወይም ዕቃ በመድኑ ውል ውስጥ ባልተመለከተ አደጋ ቢወድም በዚሁ

[63] በግርጌ ማስታወሻ ቁ.59 የተመለከተዉ።.

[64] ከላይ በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 የተመለከተው ገጽ 138-142፤ እንዲሁም በግርጌ ማስታወሻ ቁ 56 ላይ የተመለከተው ገጽ 697 እና ተከታዮቹን ገጾች ይመልከቱ።

ቁጥር ሥር በተጻፈው መሠረት ውሉን ለማስፈረስ ስለአደጋው ያስታውቅ እንደሆነ ነው እንጂ በን.ሕ.ቁ. 670/1/ ሥር የተጻፈው ግዴታ ተፈጻሚ ሆኖበት አይደለም።

በን.ሕ.ቁ. 670/1/ የእንግሊዝኛው ቅጂ ከተሄደ "... the beneficiary shall inform the insurer of any occurrence likely to render the insuerr liable..." ስለሚልና ከአማርኛው ቅጂ አነጋገር የሰፋ ስለሚሆን ማንኛውንም መድን ሰጪውን በውሉ የገባበትን ግዴታ ለመፈጸም ሃላፊ የሚያደርገው ሁኔታ መድረሱን ማስታወቅ እንደሚሆን እንረዳለን። በእንግሊዝኛው ቅጂ ከተሄደ በን.ሕ.ቁ 670/1/ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ በሕይወት ኖሬ ከተገኘሁ ይህን ያህል ብር ትከፍለኛለህ በሚል የሕይወት መድን ውል ላይና በኃላፊነት መድንም ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ሲገመት በአማርኛ ቅጂ ከተሄደ ግን የቁ. 670/1/ ተፈጻሚነት በንብረት መድንና ለሞት በሚገባ መድን ላይ ብቻ የተገደበ ይመስላል። የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የሚጠቀምባቸው ፖሊሲዎች የእንግሊዝኛውን ቅጂ ይከተላሉ። በአማርኛውና እንግሊዝኛው የን.ሕ.ቁ 670/1/ አባባል መካከል ስላለው ልዩነት ይህን ያህል ካልን ወደዋናው በዚሁ በቁጥር 670 ሥር ስለተጻፈው ግዴታ እንመለሳለን።

የደረሰው አደጋ መድን ገቢው ራሱ የተሳተፈበት ለምሳሌ መድን የተገባለት ተሽከርካሪ ሾፌር ሆኖ እየነዳ እያለ አደጋ ቢደርስ ወይም መኖሪያ ቤቱን ለእሳት ቃጠሎ መድን አስገብቶ የቃጠሎ አደጋ ሲደርስ ቤቱ ውስጥ ከነበረና ራሱ ግን ከመቃጠል ያመለጠ ከሆነ ወዘተ የአደጋውን መድረስ ማወቁ ምንም አጠራጣሪ ስላልሆነ ከአቅም በላይ በሆነ ኃይል ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ወይም አደጋው የደረሰው ከሥራ ሰዓት ውጭ ወይም በበአል ቀን[65] ካልሆነ የአደጋውን መድረስ ማስታወቅ ያለበት ወዲያውኑ[66] ነው። ምናልባት "ወይም እጅግ ቢዘገይ በአምስት ቀናት ውስጥ" የሚለው የን.ሕ.ቁ 670/1/ አባባል ከላይ ለማመልከት በተሞከረውና መድን ገቢው ራሱ በነበረበት የአደጋ ሁኔታ አሳሳች ሳይሆን አይቀርም ተብሎ ይገመታል። ሆኖም ግን አንድ መድን ገቢ አደጋው ሲከሰት ቢኖርም አደጋው በደረሰ እስከ አምስት ቀናት ውስጥ ቢያስታውቅ /ከዐቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ማጋጠም እንደተጠበቀ ሆኖ/ ከሕጉ ውጪ ስላልሆነ ሊከራከርበት ይችላል።

ሌላኛው በዚህ ርዕስ ሥር መነሳት ያለበት ነጥብ ለመድን ሰጪው አደጋ መድረሱን የማሳወቅ ሁኔታ መነሻው የመድን ገቢው የራሱ ያደጋውን መድረስ ማወቅ መሆኑን ነው። መድን ገቢው በቦታው ላይ በክስተቱ ጊዜ ኖሮ ያደጋውን መድረስ ካላወቀ ምናልባት አደጋ ደርሶ ለመድን ሰጪው ሳይነገረው ወራት ሊያልፉ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል። መድን ገቢው ያደጋውን መድረስ

---

[65] መድን ሰጪው ከሥራ ሰዓት ውጪና በበዓላት ቀናት የአደጋ ማስታወቂያን የሚቀበልበትን ሁኔታ አመቻችቶ ይህንኑ ለደምበኞቹ ካላሳወቀ በቀር

[66] "ወዲያውኑ" የሚለው አባባል ራሱ አከራካሪ ሊሆን ይችላል። ምናልባት "ሊገኝ በሚችል የተሻለ ፈጣን መንገድ" ማለት ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችል ይሆናል።

መረጃ እንደገኘ ወዲውኑ ወይም እጅግ ቢዘገይ በአምስት ቀናት ውስጥ /ከዐቅም በላይ የሆነ ሁኔታ እንደተጠበቀ ሆኖ/ ለመድን ሰጪው ማስታወቅ እንዳለበት ነው የምንረዳው። ይህንን የምንልበት ምክንያት በን.ሕ.ቁ 670/1/ አነጋገር አደጋው እንደደረሰ ወዲያውኑ ወይም እጅግ ቢዘገይ በአምስት ቀናት ውስጥ ማስታወቅ አለበት የማይል መሆኑን ለማስገንዘብ ያህል ነው። በን.ሕ.ቁ. 670/2/ ሥር እንደተጻፈው በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር የተጻፈውንና ጊዜን የሚመለከተውን አነጋገር ማስረዘም ይቻል እንደሆነ እንጂ ማሳጠር እንደማይቻል መረዳቱ ቀላል ነው።

የአደጋን መድረስ የማስታወቅን ግዴታ ከአንዳንድ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት ከሚጠቀምባቸው ፖሊስዎች አንፃር ለማየት መሞከሩ በሕጉና በተግባር በሚሠራው መካከል ስምምነትም ይሁን ልዩነት መኖሩን ስለሚጠቁም ይህን ከዚህ በታች ባጭሩ እንመለከታለን። በሠራተኞች የካሳ መድን /workmen's compensation policy/ ላይ እንደ 4ኛው ሁኔታ (condition) የሠፈረዉ በፖሊስው መሠረት ካሣ የሚያስጠይቅ ሁኔታ መድረሱን መድን ገቢው "በተቻለ ፍጥነት" ለመድን ሰጪው ማስታወቅ አለበት የሚል ሲሆን በኃይል ሠብሮ በመግባት ፖሊሲ፣ በእሳትና መብረቅ ፖሊሲ፣ እና በግልና ንግድ ተሽከርካሪዎች ፖሊሲዎች ላይ ደግሞ ካሣ የሚያስጠይቅ ሁኔታ እንደደረሰ "ወዲያውኑ" ማስታወቅ አለበት ተብሏል። የሁሉም ዓይነት አደጋ መድን ፖሊሲ /all risks policy/ በሚባለው ላይ ደግሞ መድን በተገባለት ንብረት ላይ አደጋ መድረሱን መድን ገቢው ከደረሰበት በኋላ "ተግባራዊ ሊሆን በሚችል በተቻለ ፍጥነት" /As soon as practicable/ ማስታወቅ እንዳለበት ተጽፎ እናነባለን።

በአካል ጉዳት መድን ፖሊሲ ላይ (As soon as possible after its occurrence) "አደጋው ከደረሰ በኋላ በተቻለ ፍጥነት" ተብሎ ሲጻፍ ለሞት በተደረገ የሕይወት መድን ግን ለሞቱ መንስዔ የሆነው አደጋ ከሆነ ወዲያውኑ ማስታወቅ እንደሚያስፈልግ ሲያመለክት መንስኤው አደጋ ሳልሆነ ሞት ግን በሰላሣ ቀናት ውስጥ ማስታወቅ እንደሚቻል ተጽፎአል። ይኸኛው የኋለኛው ፖሊሲ ከዐቅም በላይ የሆነውን ሁኔታም ከግምት ውስጥ ሲያስገባ ሌሎቹ ፖሊሲዎች ግን በዝምታ አልፈውታል።

ከፖሊሲዎች አኳያ ዋናው መነሳት ያለበት ነጥብ በን.ሕ.ቁ. 670/1/ ሥር "እጅግ ቢዘገይ በአምስት ቀናት ውስጥ" ተብሎ የተጻፈው አባባል በማንኛውም ፖሊሲ ውስጥ ተጽፎ አለመገኘቱንና ይህ አለመጻፉ ደግሞ የመድን ገቢውን መብት በሕግ ከተሰጠው ማጥበብ መሆኑን ነው። አደጋን በስምምነቱ መሠረት ማስታወቅ ለመድን ሰጪው በኃላፊነት መጠየቅ እንደ ቅድመ ሁኔታ /Condition precedent/ የሚቆጠር መሆኑ ባብዛኞቹ ፖሊሲዎች ላይ ሲጠቀስ በአንዳንዶቹ ግን ቅድመ ሁኔታ መሆኑ አልተጠቀሰም።[67]

---

[67] ለምሣሌ Commercial Motor Policy (third party) እና Workmen's Compensation Policy.

የመድን አገልግሎት ኢንዱስትሪ በጣም ተስፋፍቶ ባለበት በእንግሊዝ አገር ሁኔታ (Condition) ወይ "ተራ" ወይም ደግሞ ቅድመ ሁኔታ /Condition precedent/ ተብሎ የሚከፈል ነዉ። በፖሊሲዎች ላይ እንደ ቅድመ ሁኔታ ያልተመለከቱት ነገሮች የመድን ሰጪውን ኃላፊነት ሳያስቀሩ እንደሚችሉ ስንገነዘብ[68] በቅድመ ሁኔታነት የተጠቀሱት ጉዳዮች ያለመሟላት ግን መድን ሰጪው የካሣ ጥያቄ ከቀረበበት አደጋ አኳያ ብቻ ከኃላፊነት ነፃ የሚያደርጉት ናቸው። [69]

### ለ. የመድን ገቢው መብት

መድን ገቢው በውሉ የተመለከተው አደጋ መድረሱን ወይም ሌላ ማንኛውንም መድን ሰጪውን በኃላፊነት የሚያስጠይቀው ነገር መፈጸሙን የማስታወቅ ግዴታ እንዳለበት ሁሉ በውሉ መሠረት እንዲካስ ወይም ስምምነት የተደረገበት ገንዘብ እንዲከፈለው የመጠየቅ መብትም አለው። መድን ገቢው የካሣ ጥያቄውን በምን ያህል ጊዜ ለመድን ሰጪው ማቅረብ እንዳለበት በሕጉ ላይ የተመለከተ ነገር ባይኖርም በን.ሕ.ቁ. 670/1/ ሥር አደጋ መድረሱን ሲያስታውቅ በዚያው የካሣ ጥያቄውንም ያቀርባል ተብሎ በውስጠ ታዋቂነት ተካትቷል ወይም የካሣ ጥያቄን ማቅረብ ለሁለቱ ወገኖች ስምምነት የተተወ ጉዳይ ነው ማለት ይቻል ይሆናል።

በሕጉ ላይ የተባለ ነገር ባይኖርም በመድን ውሉ መሠረት ገንዘብ እንዲከፈለው ወይም እንዲካስ ጥያቄ የማቅረብ ሁኔታ ግን በሁሉም ፖሊሲዎች ላይ ተመልክቷል። በዚሁ መሠረት በአንዳንዶቹ ላይ የተጻፈውን ብንቃኝ በሠራተኞች የካሣ መድን ፖሊሲ ላይ መድን ገቢው እንዲክስ ጥያቄ እንደቀረበለት ወዲያውኑ ለመድን ሰጪው ጥያቄውን መላክ እንደለበት ሲጻፍ በኃይል ሠብሮ በመግባት ፖሊሲ ደግሞ በ5ኛው /መ/ ሁኔታ ሥር የመድን ሰጪውን ኃላፊነት የሚያስከትለው ማንኛውም ሁኔታ እንደተፈጸመ በተቻለ ፍጥነት ወይም ለማንኛውም ኃላፊነትን የሚያስከትለው ሁኔታ በደረሰ በ14 ቀናት ውስጥ የካሣውን ጥያቄ ከዝርዝር ሁኔታዎች ጋር ማቅረብ አለበት ሲል ጥያቄው በጽሑፍ ስለመቅረቡ ግን አይናገርም። የእሳትና የመብረቅ መድን ፖሊሲ አደጋው ከደረሰ በኋላ በ15 ቀናት ውስጥ ወይም እንደሁኔታው መድን ሰጪው በጽሑፍ በሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ የካሳ ጥያቄውን ማቅረብ አለበት ይልና ጥያቄውም በጽሑፍ መቅረብ እንዳለበት ያመለክታል።

### የመድን ሰጪው ግዴታ

ከዚህ በፊት ለማመልከት እንደተሞከረው የመድን ውል በመድን ገቢ ላይ ከምሥረታው ጀምሮ ተፈጻሚ ሲሆን በመድን ሰጪው ላይ ተፈጻሚ የመሆኑ ጉዳይ ግን በሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም ማለት መድን ሰጪው የውሉን

---

[68] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 ላይ የተመለከተው ገጽ 126።

[69] በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8 ላይ የተመለከተው ከገጽ 211-212።

ግዴታ እንዲወጣ የሚጠየቀው በውሉ የተመለከተው አደጋ ወይም ኃላፊነት ውሉ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ የደረሰ ከሆነ ብቻ ወይም ደግሞ ፖሊሲው መድን ገቢው እስከተወሰነ ቀን ድረስ በሕይወት ከኖረ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ከሆነ በዚያ በተባለው ቀን መድን ገቢው በሕይወት ኖሮ ከተገኘ ብቻ ነው።

በዚህ ረገድ በን.ሕ.ቁ. 663/1/ ሥር በግልጽ እንደሠፈረው ሕጉም መድን ሰጪው በውሉ ለተመለከተው አደጋ መድን ለገባው ሰው መድን እንደሚሆን ሲደነግግ በዚሁ ሕግ በቁጥር 665/1/ ላይ ደግሞ በቁጥር 663/1/ ሥር ከተጠቀመበት ቋንቋ ሻል ባለ ሁኔተ "መድን ሰጪው በውሉ ውስጥ የተመለከተው አደጋ በደረሰ ጊዜ ወይም በውሉ ውስጥ የተስማሙበት ቀን በደረሰ ጊዜ የተሰማሙበትን ገንዘብ በውሉ በተወሰነ ቀን መክፈል ይገባዋል" ይላል።

ሕጉ መድን ሰጪው በፖሊሲው ላይ የተመለከተው አደጋ ሲደርስ ወይም ጊዜ ሲሞላ በውሉ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ መክፈል አለበት ይበል እንጂ ሁል ጊዜም በውሉ የተመለከተው አደጋ በደረሰ ጊዜ ወይም ጊዜ ከሞላ መካስ ወይም የተስማሙበትን ገንዘብ ለመድን ገቢው መክፈል አለበት ማለቱ ግን አይደለም። በን.ሕ.ቁ. 663/1/ እና 665/1/ ላይ የተቀመጡት ግዴታዎች የሚታዩት ከሌሎች የንግድ ሕግ ቁጥሮች ጋርና አዛዥ የሕግ አንቀጾችን ባልተቃረነ አኳኋን ተዋዋይ ወገኖች በተሰማሙበት መሠረት ስለሆነ የን.ሕ.ቁ. 663/1/ እና 665/1/ በመድን ሰጪው ላይ የመጠየቅ ግዴታን ስለጣሉ ብቻ ይከሳል ማለት አይደለም።

ይህን በምሳሌ ለማስረዳት ብንሞክር ለአንድ መኖሪያ ቤት ለእሳት አደጋ መድን ተገብቶለት ኖሮ የመኖሪያ ቤቱ ከመድን ውሉ ምሥረታ በኋላ በእሳት አደጋ መውደሙ በማያከራክር ሁኔታ ቢረጋገጥ በአንድ በኩል የን.ሕ.ቁ. 663/1/ እና 665/1/ ለብቻ ሲታዩ መድን ሰጪው ካሣ ለመክፈል መገደዱ ምንም የማያጠራጥር ሲሆን በሌላ በኩል ግን የደረሰው የቃጠሎ አደጋ መንስዔ በመድን ገቢው ሆን ተብሎ የተደረገ ጥፋት ምክንያት የመጣ ከሆነ ተቃራኒ ስምምነት እንኳን ቢኖር መድን ሰጪው በሃላፊነት እንደማይጠየቅ በን.ሕ.ቁ. 663/3/ ሥር ተመልክቶአል። በሌላ አነጋገር ምንም እንኳን በመድን ገቢው ላይ የደረሰው ጉዳት ተፈርቶ መድን በተገባለት አደጋ ቢሆንም መድን ገቢው የመድኑን ፖሊሲ ገንዘብ አገኛለሁ በሚል ቀቢፀ ተስፋ ተነሳስቶ ሆን ብሎና አስቦ መድን የተገባለት ጉዳት እንዲደርስ ቢያደርግ መድን ሰጪው የመካስ ግዴታው ይነሳለታል ማለት ሲሆን፣ ከሕይወት መድን አኳያም ሲታይ መድን ገቢው ሆነ ብሎ ራሱን ቢገድል[70] ወይም ደግሞ አንድ የሕይወት መድን ተጠቃሚ መድን ገቢውን ሆን ብሎ ገድሎ ለዚህም በወንጀል ፍርድ ቤት ጥፋተኛነቱ ቢረጋገጥበት ውሉ ዋጋ እንደሌለው ሕጉ በግልጽ አስቀምጧል።[71]

---

[70] የን.ሕ.ቁ. 699

[71] የን.ሕ.ቁ. 700

የን.ሕ.ቁ. 663/3/ 699 እና 700 የሚያንፀባርቁት ሐሳብ "ex turpi causa non oritur actio" ከሚባል የላቲን አባባል የመጣ ሲሆን ትርጉሙም "no action can arise from a wrongful cause" ሆኖ በአማርኛ "ክስ የማቅረብ መብት ከወንጀል ድርጊት አይመነጭም" ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፡፡ ይህ ከዚህ በላይ የተነገረው የላቲን አባባል በተግባር ተፈጻሚ ሲሆን "ማንኛውም ሰው ከወንጀል ድርጊት ተጠቃሚ መሆን የለበትም" በሚል የተወሰደ ሲሆን በእንግሊዝኛው "A man may not profit from his own wrong or crime" የሚል መርህ ሆኖ ይሠራበታል፡፡[72] በሌላ አነጋገር የን.ሕ.ቁ. 663/3/፣ 699 እና 700 የፐብሊክ ፖሊስ ድንጋጌዎች ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡በዚህ ረገድ ጆን በርድስ እንዲህ ይላሉ፡፡ "... (He) (The insured) cannot recover if the loss was caused by his deliberate act. This may be simply the true construction of an insurance contract or it may alternatively be regarded as the application of public policy".[73]

ይሁን እንጂ በመድኑ ውል ፖሊሲ ውስጥ ተቃራኒ ስምምነት ካልኖረ በስተቀር በን.ሕ.ቁ. 663/2/ መሠረት መድን የተገባለት አደጋ የደረሰው መድን በገባው ሰው ቸልተኝነት[74] ወይም ባልታበሰ አደጋ ከሆነ መድን ሰጪው በውሉ መሠረት የመካስ ግዴታ ይወድቅበታል፡፡ ከዚህ በላይ ለማመልከት እንደተሞከረው መድን ገቢው በገዛ ራሱ መሠሪ ድርጊት መድን የተገባለት አደጋ እንዲደርስ ቢያደርግ አይካስም ብሎ ሲል ሆን ብሎ ሳይሆን በመድን ገቢው ስሕተት ወይም ቸልተኝነት ለሚደርሰው አደጋ ግን መድን ሰጪው የመካስ ግዴታ እንደሚወድቅበት ሕጉ ደንግጉአል፡፡[75] "ተቃራኒ ስምምነት ካልኖረ" የሚለው በን.ሕ.ቁ. 663/2/ ሥር ሠፍሮ ያለው ሐረግ መድን ሰጪው በመድን ገቢው ቸልተኝነት ምክንያት የደረሰውን ጉዳት አልክስም ብሎ በፖሊስዎች ውስጥ እንዲያስገባ ሰፊ ዕድል ሲሰጠው በመድን ገቢው ቸልተኝነት ለደረሰው ጉዳት አልጠየቅም የሚል የውል ቃል በፖሊሲዎች ላይ ከገባ ለመድን ሰጪው በኃላፊነት መጠየቅ የሚቀረው ጉዳት የደረሰው ባልታሰበ አደጋ "accident" ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህ ማለትም የጉዳት ባልታሰበ አደጋ መድረስ ከቸልተኝነትም ሆን ተብለው ከሚደረጉትም ሁኔታዎች ዉጪ መሆኑን ሲጠቁም "ባልታሰበ አደጋ" የሚለው ጉዳቱ የደረሰው ባልተጠበቀ

[72] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8፣ ገጽ 203፡፡

[73] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 8፣ ገጽ 203፡፡

[74] አንድ መድን ገቢ ከአእምሮ ሕመም የተነሳ ወይም በቸልተኝነት ራሱን ቢገድል የመድን ውሉ ተጠቃሚ የፖሊሲውን ገንዘብ አያገኝም ለማለት አይቻልም፡፡ /የን.ሕ.ቁ.669/ ያንድ የሕይወት መድን ተጠቃሚም መድን ገቢውን ሆን ብሎ ሳይሆን በስሕተት ቢገድል የን.ሕ.ቁ. 700 ተፈጻሚ ስለማይሆን የፖሊሲውን ገንዘብ ያገኛል፡፡

[75] ምንም እንኳን በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1795 እና 1796 መሠረት ከውል ግንኙነት አኳያ የ "ጥፋት" ፅንስ ሐሳብ ቢኖርም በዚሁ ሕግ ከውል ዉጪ ኃላፊነትን አስመልክቶ በቁጥር 2029 ላይ ጥፋት ሲባል ታስቦ በሚሠራ ወይም በቸልተኝነት በሚፈጸም ተግባር ሊደረግ እንደሚችል ተጽፎአል፡፡ ከወንጀል አኳያም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 57 ላይ እንደተመለከተው አንድ ሰው በወንጀል የሚጠየቀው ሆን ብሎ አስቦ ሲያጠፋ ወይም በቸልተኝነት ሲያጠፋ ብቻ ሲሆን ባልታሰበ ደጋ የሚፈፀም ሊያስቀጣ የሚችል ድርጊት በወንጀል እንደሚያስጠይቅም ተደንግጉአል፡፡

ፍጹም ዱብዕዳ በሆነ ሁኔታ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በን.ሕ.ቁ. 663/2/ መሠረት "ባልታሰበ አደጋ" ለሚደርሱ ጉዳቶች መድን ሰጪው እንዳይጠየቅ በውል ግዴታውን ሊያስቀር እንደሚችል ተመልክቷል።

በን.ሕ.ቁ. 663/2/ ሥር "ተቃራኒ ስምምነት ካልኖረ" የሚለው ሐረግ በቸልተኝነት ሽፋን ሰዎች ግዴለሽ ሆነው ለጉዳት መድረስ መንስዔ እንዳይሆኑ በውል ስምምነት ለመከላከል ካልሆነ በስተቀር ሚናው ባጠቃላይ በመድን ገቢው ቸልተኝነት የሚደርሱትን ጉዳቶች ከመድን ሰጪው ኃላፊነት ውጭ ለማድረግ ነው ተብሎ አይገመትም። ባልታሰበ አደጋ የሚደርሱትን ጉዳቶች በውል ከመድን ሰጪው ኃላፊነት ውጪ ማድረግም ጨርሶ መድንን ትርጉም የለሽ ወደ ማድረጉ ስለሚያቀርበው መድን ሰጪው ይጠቀምበታል ብሎ መገመት አዳጋች ይሆናል።

መድን የተገባለት አደጋ የደረሰውና በዚሁ ምክንያት በመድን ገቢው ላይ ጉዳት ያስከተለው በራሱ መሠሪ ድርጊት ወይም በርሱ ቸልተኝነት ሲሆን ምን ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል በን.ሕ.ቁ. 663/2/ እና /3/ ላይ ሲደነገግ ራሱ መድን ገቢው ሳይሆን እርሱ ኃላፊ የሚሆንላቸው ሰዎች ባደረጉት ጥፋት ለሚደርስ ጉዳትም መድን ሰጪው በን.ሕ.ቁ. 664/1/ ሥር በተጻፈው መሠረት ኃላፊ ተደርጉአል።

እነኚህ መድን ገቢው ኃላፊ የሚሆንላቸው ሰዎች እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ በሕጉ ላይ በግልጽ የተመለከተ ነገር ባይኖርም ምናልባት በን.ሕ.ቁ. 683/3/ ሥር የተዘረዘሩት ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ የሚል ግምት አለ። የመድን ገቢዋ ባል ወይም የመድን ገቢው ሚስት በ.ን.ሕ.ቁ. 683/3/ ሥር ከተዘረዘሩት ሰዎች ውስጥ ሊደመር ወይም ልትደመር ስትችል በሌላ በኩል ግን ሚስትን ከመድን ገቢ ባል ወይም ባልን ከመድን ገቢዋ ሚስት ምን ለያት ወይም ለየው? በሚል ስሜት ተትቷል ወይም ተትታለች ብሎ ለማለት ይቻል ይሆናል።

በን.ሕ.ቁ. 664/1/ ሥር መድን ገቢው ኃላፊ የሚሆንላቸው የተባሉት ሰዎች በፍ.ብ.ሕ.ቁ 2124 እና ተከታታዮቹ ሥር የተመለከቱት ሊሆኑ እንደሚችሉም ይገመታል። የመድን ሰጪው በን.ሕ.ቁ. 664 ተጠያቂ መሆን በዚሁ ቁጥር በንዑስ ቁጥር /1/ ሥር የተመለከቱት ሰዎች ያደረጉት ጥፋት ዓይነትና ክብደት ሳይታይ ማለትም ጉዳት ያስከተለውን ጥፋት ያደረሱት ሆን ብለው ይሁን በቸልተኝነት እግምት ውስጥ ሳይገባ መድን ሰጪው ተጠያቂ ይሆናል። ሆኖም መድን ሰጪውን የመዳረግ መብት በተመለከተ የንግድ ሕጉ የሚለዉን ማጤኑ ጠቃሚ ይሆናል።[76]

---

[76] የን.ሕ.ቁ. 683/3/ን ይመልከቱ።

ሌላው ሁለቱን ተዋዋይ ወገኖች የሚመለከት ዐቢይ ጉዳይ የይርጋ ጉዳይ ነው። የይርጋን ጉዳይ ከመድን ሕግና ውል አኳያ ማየት ከመጀመራችን በፊት በፍትሐ ብሔር ሕግ የውል ጠቅላላ ሕጎች ክፍል ውስጥ ስለጉዳዩ በተጻፈው በቁጥር 1845 ብንጀምር "ሕግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር ውል እንዲፈጸም ወይም ካለመፈጸሙ የተነሣ ለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንዲፈርስ የመጠየቅ መብት በአሥር ዓመት ይርጋ" ይቀራል" ይላል። ምንም እንኳን ማንኛውንም ውል በተመለከተ የፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1845 ተፈጻሚ ሊሆን ቢችልም በዚሁ ቁጥር "ሕግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ" የሚለው ሐረግ አልፎ አልፎ ሕግ የሚያስቀምጠው አጠር ያለ ወይም ረዘም ያለ የይርጋ ዘመን ካለ ይኸው የተጠበቀ መሆኑን ለማመልከት ነው። በሌላ አነጋገር ልዩ ልዩ ሕጎች በተለይም ደግሞ በፍትሐ ብሔር ሕግ አምስተኛ መጽሐፍ፣ በንግድ ሕግና በባሕር ሕግ ውስጥ ባሉት ልዩ ውሎች ውስጥ ሕግ ስለይርጋ በሌላ አኳኋን ወስኖ ቢገኝ በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1845 እና 1676/2/ መሠረት በልዩነታቸው ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል ማለት ነው።

በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1845 ሥር ከተደነገገው የይርጋ ዘመን ለየት ያለ ውሣኔ ከተሰጠባቸው ግንኙነቶች መካከል አንዱ ከመድን ውል[77] በሚመነጩ መብቶችና ግዴታዎች ላይ ሲሆን ሌሎችም በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 2143 ሥር ከውል ውጪ ኃላፊነትን በሚመለከት እንዲሁም ከቼክ ጋር በተያያዘ ያለውን የይርጋ ዘመን በን.ሕ.ቁ.881 እና 882 ሥር የመለከቱት እንደምሣሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ከዚህ ጹሑፍ አኳያ ለማየት የሚፈለገው የመድን ውል ግንኙነት የሚፈጥራቸው መብትና ግዴታዎች በይርጋ የሚታገዱት እንዴት ነው የሚለውን ጥያቄ ስለሆነ ይህንኑ ከዚህ በታች ባጭሩ እንመለከታለን።

የመድንን ውል የሚመለከተው የይርጋ ሕግ የን.ሕ.ቁ. 674 የሚከተለዉን ይደነግጋል፦

> "በኢንሹራንስ ውል ምክንያት የሚቀርብ ማንኛውም ክስ የሚታገደው ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት ከተደረገበት ወይም በጉዳዩ ቅጥም ያላቸው ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ዓመት በኋላ ነው"

የኢትዮጵያ የባሕር ሕግ ከንግድ ሕጉ ጋር ሲነጻፀር ስለ ይርጋ ዘርዘር ያሉ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል። የባሕር ሕጉ የይርጋ ድንጋጌዎች ይርጋ የሚቋረጥባቸዉን ሁናቴዎች ጨምረዉ መያዛቸዉ አጽንኦት ሊሰጠዉ ይገባል። ከንግድ ህጉ በተለየና ግልጽ በሆነ ቋንቋ የኢትዮጵያ የባሕር ሕግ በቁ. 348 ላይ

[77] የን.ሕ.ቁ. 674

"ከኢንሹራንስ ዉል የሚመነጩ ክስ የማቅረብ መብቶች ሁሉ በሁለት ዓመት ይርጋ ይታገዳሉ" በማለት ይደነግጋል::[78]

የን.ሕ.ቁ. 674 ሌሎቹ ንዑስ ቁጥሮች የሚሉትን ወደኋላ ላይ ለማየት ትተናቸው በንዑስ ቁጥር /1/ ላይ ብናተኩር ሁለት ነጥቦችን እናያለን:: እነኚህም

1) ከመድን ውል በተነሣ የሚቀርብ ማንኛውም ክስ የይርጋው ዘመን ሁለት ዓመት መሆኑ፣
2) ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው:-
ሀ/ ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ወይም
ለ/ በጉዳዩ ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ቀን ጀምሮ

መሆኑን ነው::

ከነኚህ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ሁለት ነጥቦች የሚያከራክር ሁኔታን የሚያስነሱት በሁለተኛው ነጥብ /ሀ/ እና /ለ/ ሥር የተነገሩትና የይርጋው ዘመን መቆጠር የሚጀምርባቸው ሁናቴዎች ናቸው:: የአንድ መድን ገቢ ክስ በሁለት ዓመት ይርጋ ይታገዳል ለማለት ምን ሲሆን ነዉ ቆጠራው የሚጀምረው "ለክሱ ምክንያት የሆነው ጉዳት ከደረሰበት" ነው የምንለዉ? ምን ሲሆን ቆጠራው የሚጀምረው በጉዳዩ ጥቅም ያላቸው ወገኖች ስለአደጋው ካወቁበት ቀን ጀምሮ ነው የምንለዉ? ከዚህ በላይ በቁጥር 2 (ሀ) ላይ የተመለከተውን የይርጋው ዘመን መቆጠር የሚጀምርበትን ጊዜ ሕግ አውጪው ከራሱ ከመድን ገቢው አኳያ እንዲታይ ፈልጐ በ 2 (ለ) ላይ የተመለከተውን ደግሞ ከሌሎች በጉዳዩ ጥቅም ካላቸው ሰዎች ስለጉዳቱ ማወቅ አንፃር ብቻ እንዲታይ ፈልጐ ነው ለማለት ይቻል ይሆን?

የደረሰውን አደጋ /ጉዳት/ የማወቅ ጉዳይ ከሆነ መድን ገቢውም ቢሆን መድን የተገባለት አደጋ መድረሱን ካላወቀ በን.ሕ.ቁ. 670 ላይ ያለውን ግዴታውን እንኳን ሊወጣ አይችልም፣ የካሣ ጥያቄም ማቅረብ አይችልም:: ምናልባት ሕግ አውጪው ከዚህ በላይ በቁጥር 2 (ሀ) እና (ለ) ላይ ያስቀመጣቸው ሁለት የተለያዩ የሁለት ዓመት ይርጋ መቆጠር የሚጀምርባቸው ሁኔታዎችን ያሠፈረው ከ "ሀ" አንፃር የመድን ገቢው የአደጋን መድረስ ማወቅ ምንም መጠራጠር አያስፈልግም /it should be taken for granted/ ከሚል የተነሳ ነው ሊባል ይችል ይሆናል:: ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ መቶ በመቶ ትክክል ነው ለማለት አያስደፍርም:: ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁለተኛው ነጥብ "ለ" ላይ "በጉዳዩ ጥቅም ያላቸው ወገኖች ጉዳቱን ካወቁበት ጀምሮ" የተሰኘው ምናልባት እነኚህ በጉዳዩ ጥቅም ያላቸው ሰዎች ስለአደጋው ቆይተው ሊያውቁ ስለሚችሉ[79] መብታቸዉን ላለማጥበበ ይርጋው

---

[78] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የባሕር ሕግ ፣ነጋሪት ጋዜጣ ቁ. ፩፣በ1952 ዓ.ም. በተለይ የወጣ፣ አዲስ አበባ::

[79]ከመድን ውሉ ጋር በተያያዘ ጥቅም ያላቸው 3ኛ ወገኖች ያደጋውን መድረስ ሳያውቁ ሊቆዩ ይችላሉ:: በመሆኑም የነርሱን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲል ሕግ አውጪው እነኚህን በተመለከተ የሁለቱ ዓመት ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው እነርሱ ያደጋውን መድረስ ካወቁበት እንጂ አደጋው ከደረሰበት ቀን አለመሆኑን ደንግጓል::

መቆጠር የሚጀምረው አደጋው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን እነርሱ ካወቁበት ቀን ጀምሮ ነው ብሎ ለማለት ፈልጎ ይሆናል ሕግ አውጪው መቼም በ "ለ" ላይ ያለውን ሁኔታ አስረድቶ በይርጋ ምክንያት ክሱ ይታገዳል ለማስኘት መድን ሰጪው ያለበትን ፍዳ መገመቱ ከባድ አይደለም፣ በተቃራኒዉ አደጋ የደረሰበትን ቀን ማስረዳቱ ቀላል ነው።

ሌላው በን.ሕ.ቁ. 674/1/ሥር አከራካሪ ሊሆን የሚችለው ነጥብ "ጉዳት" ለሚለው ቴክኒካዊ ቃል የሚሰጠው ትርጉም ነው። ከዚህም አኳያ ለመሆኑ "ጉዳት" የተባለው ቃል መድን ሰጪው በመድን ገቢው ላይ ለአረቦን ክፍያ የሚያቀርበውን ክስ በን.ሕ.ቁ. 674/1/ ሥር ከተመለከተው የይርጋ ዘመን ውጪ ያደርገው ይሆን? ሌሎችስ "ጉዳትን" የማይመለከቱትን መድኖች ይጠቀልል ይሆን? የሚሉትን ጥያቄዎች ሊያስከትል ይችላል። በአንድ በኩል የን.ሕ.ቁ. 674/1/ የእንግሊዝኛ ቅጂ "From the occurrence giving rise to the claim" ሲል አባባሉ ምናልባት ሰፋ ያለና ማንኛውም ከመድን ውል የሚነሣ ክስ ወደማለት ይወስዳል ሊባል ሲችል በሌላ በኩል "occurrence" የሚለው ቃል ዞሮ ዞሮ የአደጋን መድረስ /materialization of the risk insured/ የሚያመለክት በመሆኑ የእንግሊዝኛውም ቅጂ "ጉዳት" የሚለውን ቃል ከተጠቀመው ከአማርኛው ቅጂ አልራቀም ለማለት ይቻላል። የሆነ ሆኖ "occurrence" "ጉዳት" ከሚለው ቃል ሰፋ ማለቱ ብዙም አያከራክርም።

በን.ሕ.ቁ. 674/1/ "ጉዳት" የሚለው ቃል ከተወሰደ ለተወሰነ ጊዜ በሕይወት ኖሬ ከተገኘሁ ይህን ያህል ትከፍለኛለህ የሚል ስምምነት የሚደረግበትን የሕይወት መድን ዘርፍ እንደማይጨምር መከራከር ይቻላል፡፡ ከሁሉም ይበልጥ ግን መድን ሰጪው የተወዘፈ አረቦን እንዲከፈለው ጠይቆ በአንድ ወሩ የፋታ ጊዜ ውስጥ ካልተከፈለው የሚያቀርበው ክስ በን.ሕ.ቁ. 674/1/ ይርጋ ይታገዳል? አይታገድም? የሚለው ጥያቄ ጉዳት ከሚለው ቃል አኳያ እንዴት ይታያል የሚል አከራካሪ ጥያቄ ያስነሳል።

የመድን ሰጪው ውዝፍ አረቦን እንዲከፈለው ጠይቆ ያለማግኘት እንደ "ጉዳት" ሊታይ ይችል ይሆን? በእንግሊዝኛው ቅጂ መሠረት (is it an occurrence?) ተብሎ ሲጠየቅ "ጉዳት" የሚለው ያማርኛ ቃልና "Occurrence" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በጠባቡ ከተወሰዱ መልሱ አሉታዊ ሲሆን በሰፊው ከተወሰዱ ግን መልሱ አዎንታዊ ሊሆን ይችላል።

በፍ.ብ.ሕ.ቁ. 1845 አባባል ከተሄደ የመድን ሰጪው ውዝፍ አረቦን እንዲከፈለው ጠይቆ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ያለማግኘት እንደ "ጉዳት" የማይታይበት ምንም ምክንያት የለም። በዚህ ረገድ "ጉዳት" የሚለው ቃል "occurrence" ወይም risk materialization ን የሚመለከት ሳይሆን "damage" የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል

ስሜት ይዞ ነው፡፡[80] በመሆኑም ወይ አረቦኑ መከፈል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ [81] በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ መድን ሰጪው ክስ ካላቀረበ ይርጋ ያግድበታል ወይም ደግሞ በን.ሕ.ቁ. 663/3/ የተጻፈውን ከግምት ውስጥ በማስገባት አረቦን ከማስከፈል አንፃር ይርጋ መቆጠር መጀመር ያለበት የአንድ ወሩ የፋታ ጊዜ ካለቀ ጀምሮ መሆን አለበት ብሎ መከራከር የሚቻል ይመስላል፡፡

በንግድ ህጉ ሊያከራክር እንደሚችል የተጠቆመዉ አረቦንን ስለሚመለከተዉ ይርጋ በባሕር ሕጉ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ቢያንስ ቢያንስ የባሕር ሕጉ የይርጋ ዘመኑ ከመቼ ጀምሮ መቆጠር እንዳለበት በመደንገግ ከንግድ ሕጉ ተሽሏል፡፡ በባሕር ሕጉ በቁ. 349 ላይ አረቦን ለማስከፈል የይርጋ ዘመን በዚሁ ህግ በቁ. 348 ሥር በተደነገገዉ እንደሚመራ ታሳቢ በማድረግ ይልቁንም አከራካሪ ሊሆን የሚችለዉንና አረቦንን ከማስከፈል አኳያ የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምረዉ ከመቼ ጀምሮ ነዉ? የሚለዉን ጥያቄ ይመልሳል፡፡

የባሕር ሕጉ ይህን አከራካሪ ነጥብ በሚመለከት እንደሚከተለዉ ደንግጓል፦

> የኢንሹራንስ ገንዘብ (ፕሪሚየም) አከፋፈልን የሚመለከተዉ የክስ ማቅረብ መብት ይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምረዉ የዉሉ ስምምነት ተቀባይነት ካገኘበት ቀን አንስቶ ነዉ፡፡[82]

የማንኛውም ከመድን ውል በተነሣ ለፍርድ ቤትም ሆነ ለግልግል ዳኝነት መድረክ የሚቀርብ ክስ ከይርጋ አንፃር በ.ን.ሕ.ቁ. 674 መገዛት አለበት የሚለው ጠንካራ ክርክር መሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

በን.ሕ.ቁ. 674/2/ ሥር ወደተጻፈው ስንመለስ የተሸሸገ ወይም በሐሰት የተሰጠ መግለጫ ካጋጠመ የሁለት ዓመቱ የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምረው መድን ሰጪው ይህን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ነው ይላል፡፡ በዚህ ንዑስ ቁጥር ሥር ያለው የይርጋ ዘመን መቆጠር የሚጀምርበት ሁኔታ ቀደም ብለን ባየነው የን.ሕ.ቁ. 668/2/ /ሀ/ ሥር ከተጻፈው ጋር አብሮ መታየት ያለበት ይመስላል፡፡ በነገራችን ላይ የን.ሕ.ቁ. 674/2/ ተፈጻሚነቱ በመድን ሰጪው ላይ ብቻ እንደሆነ አድርጐ ነው ሕጉ ያስቀመጠው፡፡ ነገር ግን ከመድን ውል ረገድ ተፈጻሚነቱ በሁለቱም

---

[80] ጉዳት ወይም በእንግሊዝኛው "damage" የሚለው ቃል በሰው ወይም በንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት የሚያመለክት ሲሆን ከሕግ አኳያ ትርጉሙ ግን ሰፋ ብሎ የገንዘብ ኪሣራንም የሚጨምር ስለሆነ ሊከፈለው ይገባ የነበረው አረቦን ሳይከፈለው ያደጋውን ሃላፊነት ላጭር ጊዜም ቢሆን የተሸከመው መድን ሰጪ አረቦኑን ባለማግኘቱ ኪሣራ (damage) ደርሶብኛል በማለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

[81] አረቦን ሲል እዚህ ጋር የማሳደሻ ወይም የማስቀጠያ አረቦንን የሚመለከት ይመስላል፡፡ ስለሆነም ይርጋው መቆጠር የሚጀመረው ማሳደሻው ወይም ማስቀጠያው አረቦን ሊከፈል ይገባ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ነው ብሎ ማሰብ ይቻል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህ ከን.ሕ.ቁ. 666/3/ አኳያ ሲታይ ብዙም ጠንካራ ክርክር አይመስልም፡፡

[82] የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የባሕር ሕግ ፣ነጋሪት ጋዜጣ ቁ. ፩፣በ1952 ዓ.ም. በተለይ የወጣ፣ አዲስ አበባ ቁ 349፡፡

ተዋዋይ ወገኖች ላይ ነው።[83] በኢትዮጵያ የመድን ሕግ ውስጥ በግልጽ ባይቀመጥም የፍጹም ቅን ልቡና ጉዳይ በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ላይ ተፈጻሚ መሆኑን የሚጠቁሙ የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች አሉ።[84]

ከመድን ውል አንፃር የይርጋን ጉዳይ ከማጠቃለላችን በፊት በን.ሕ.ቁ. 674 የተመለከተው የይርጋ ዘመን በምን በምን ምክንያቶች እንደሚቋረጥ በንግድ ሕጉ ላይ የተባለ ነገር እንደሌለ መገንዘብ ያሻል። የንግድ ሕጉ ከዚህ አኳያ ዝም ከማለቱ የተነሳ የካሣ ጥያቄውን ለመድን ሰጪው ያቀረበ አንድ መድን ገቢ መድን ሰጪው የካሣ ጥያቄውን ተቀብዬአለሁ አልተቀበልኩም ብሎ ለማስታወቅ ቢዘገይም ይህ መዘግየት የይርጋ መቆጠሩን ያቋርጣል ካልተባለ በስተቀር የግድ በ.ን.ሕ.ቁ. 674/1/ መሠረት የሁለት ዓመቱ ጊዜ ከማለፉ በፊት መክሰስ እንደሚኖርበት እንረዳለን። ይሁን እንጂ ደግሞ ሳቀረበው የካሣ ጥያቄ ከመድን ሰጪው የእምቢታም ይሆን የእሺታ መልስ ሳይገኝ ክስ ለማቅረብ መድን ገቢው በጣም እንደሚቸገር መገመቱ ቀላል ነው።

## ማጠቃለያ

በዚህ ጽሑፍ በንግድ ሕጋችን ውስጥ የሚታዩትን መድንን የሚመለከቱአንዳንድ አከራካሪ ነጥቦችን ለመጠቆም ሙከራ ተደርጓል። ከመድን ግንኙነት የተነሣ የሚከሰቱ ችግሮች ግን ሙሉ በሙሉ የተከሰቱት ወይም የሚከሰቱት ከሕጉ ድክመት የተነሣ ብቻ ባለመሆኑ ሌሎች ከግምት ውስጥ መግባት ስላለባቸው ችግሮች መጠቆሙ ወደፊት መፍትሔ ከመሻቱ ረገድ ጠቃሚና አስፈላጊ ይሆናል። በዚሁ ስሜት አንዳንዶቹን ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

- በመሠረቱ የመድን ውል እኩል ባልሆኑና እኩል ናቸው ተብለው በማይገመቱ ወገኖች መካከል የሚደረግ ውል ነዉ፣
- ከተዋዋይ ወገኖች እኩል ያለመሆን በተጨማሪ ደግሞ የመድን ውል በአንድ ወገን ማለትም በመድን ሰጪው የሚዘጋጅ በመሆኑና adhesive contracts ከሚባሉት ውሎች እንደ አንዱና ዋነኛው የሚቆጠር ነዉ፣
- ባንድ ወገን የሚዘጋጅን ውል አዘጋጁ ወገን ለራሱ በሚያመች ሁኔታ የሚያዘጋጀው ነዉ፣
- ቀደም ሲል በዚሁ ጽሑፍ ውስጥ እንደተገለጸዉ በሀገራችን ውስጥ ያሉ መድን ሰጪዎች የሚጠቀሙባቸው የመድን ውሎች የተወሰዱት የኮመን ሎው የሕግ ሲስተም ከሚከተሉት አገሮች በተለይ ደግሞ ከእንግሊዝ አገር

[83] የመድን ውል የፍጹም ቅን ልቡና ውልነት ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተፈፃሚነቱ በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ማለት በመድን ሰጪውና በመድን ገቢው ላይ ነው። ምናልባት የ.ን.ሕ. ቁ. 674/2/ ከመድን ሰጪው አንፃር ብቻ እንደሚያገለግል ተደርጐ የተፃፈው ብዙም መድን ገቢው የሚጠቀምበት ስላልሆነና ባብዛኛው አታሎኛል ውሉ ፍርስ ነው ይባልልኝ ወይም ጨርሶ ያልተገለፀ ወይም በትክክል ያልተገለፀ ማቴሪያል ፋክት አለና ውሉ ይፍረስልኝ ብሎ ጥያቄ የሚያቀርበው መድን ሰጪው ስለሆነ ይሆናል።

[84] ለምሣሌ የን.ሕ.ቁ. 680 በተለይም ንዑስ ቁጥር /1/ን ይመልከቱ።

መሆኑንና በአንፃሩ የመድን ሕጋችን የተወሰደው ባብዛኛው የሲቪል ሎው ሲስተም ከሚከተሉት አገሮች በመሆኑ በሕጉና መድን ሰጪዎቹ በሚጠቀምባቸው ፖሊስዎች መካከል ያለመጣጣም አለ፣

- ለጊዜው ወደ አማርኛ ተተርጉሞ በሥራ ላይ ካለው የሕይወት መድን ፖሊሲ በስተቀር ሌሎች ፖሊሲዎች የተዘጋጁት በእንግሊዝኛ ቋንቋ በመሆኑና በፖሊሲዎች ውስጥ ሰፍረው የምናገኛቸው ቴክኒካዊ ቃላትና ፅንሰ ሐሳቦች እንኳንስ ላልተማረ ለተማረ መድን ተቀባይ እንኳን በቀላሉ የማይገቡ ናቸው።

ከላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎች ችግሮችን ለመቅረፍ የመድን ሰጪዎቹ የራሳቸዉ ሚና ቀላል እንደማይሆን ቢገመትም የመድንን ሥራ የሚቆጣጠረው መንግስታዊ አካልም ብዙ ይጠበቅበታል። ከዚህ በላይ ከተጠቀሙት ችግሮች አኳያ ከሁሉም በላይ ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉት ፍርድ ቤቶች መሆናቸዉን በተለይም ገዢ ሊሆኑ የሚችሉትን ዉሳኔዎች የሚሰጠዉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ነዉ። ጉልቶ የሚታየውም ከመድን ውሎች አተረጓጎም አንፃር ሆኖ ከተቆጣጣሪው ባለስልጣን አስተዳደራዊ ቁጥጥር በተጨማሪ በመድን ሥራ ዘርፍ ከፍተኛ የዳኝነት ቁጥጥር አስፈላጊ መሆኑ አከራካሪ አይደለም።